# የቤተክርስቲያን ተከላ

# አገልጋዮች ፊትፊት (የስልጠና ጊዜ)

## የአሰልጣኞች መመሪያ

## ገለፃ

የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ፊትፊት ማለት፡- ቤተክርስቲያንን ለሚተክሉ አገልጋዮች የሚሰጥ የስልጠና ሞጁል ሲሆን፤ አዲስ የእምነት ማህበረሰብ የመጀመር አስፈላጊ ገፅታዎችን ሁሉ እንዲገነዘቡ ለማስቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። በተለምዶ በሁለት ወይንም በሶስት ቀኖች ስልጠና ይሰጣል፤ ሆኖም ቤተክርስቲያን የሚተክሉ አገልጋዮች አንዳንዴ ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን አዲስ የእግዚአብሔርን መንግስት ቤተክርስቲያን የሚተክሉበትን አሰር የተለያዩ ገጽታዎች ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ይበረታታሉ። በአንድ ላይ በሚኖረን ጊዜ ስለትምህርቱ ይዘት ብቻ ሳይሆን፤ አንዳችን ከሌላችን የምንማርበት፣ በጋራ የምንጸልይበት፣ ሃሳባችንን የምንገልጽበት እና የእግዚአብሔርን ለመስማት ራሳችንን የምናስለጥንበት ጊዜ ነው። በመልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ አገልግሎት ይህን ስልጠና የሚሰጡት አገልጋዮች የቤተክርስቲያ ተከላ ስልጠና ሞጁላር በሆነ ይዘት ስልጠና መስጠትን እንደመልካም አጋጣሚ የሚቀጥሩ እና በዚህም ስልጠና ውስጥ ለመሳተፍ ደስተኛ እደሆኑ ለማስገንዘብ ነው። ልምድ ላካበተና ወደፊት ቤተክርስቲያን ለመትከል ለተጠሩ አገልጋይ ይህ የስልጠና ጊዜ ግልጥነት እና ትክክለኛ አመለካከት የሚሰጥ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።

Received Feb. 29, 2020

multiplication network

*more churches, stronger churches*

# አጠቃላይ መመሪያዎች

ይህ አሰልጣኞች ማኑዋል የተሳታፊዎችን ማኑዋል ውስጥ ያልተካተቱ አሳችን አካቶ ቀርቧል:: ደመቅ ብለው የተጻፉት ቃላቶች በሙሉ በተሳታፊዎች ማኑዋል ውስጥ ለሚገኙ ባዶ ቦታዎች መልስ ናቸው:: በነዳጉ ላይ ያሉት መስመሮች በሁለቱም መመሪያዎች ለራሳችሁ ማስታወሻዎች ጥያቄዎች ሃሳቦች እና ምክሮች ወዘተ መጻፊያ ናቸው:: ልክ እንደተማሪው መመሪያ የአስተማሪውም መመሪያ ተመሳሳ የገጽ ቁጥሮች እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል::

የሚከተሉት ክፍሎች በተሳታፊዎች ማኑዋል ብቻ የሚገኙ ናቸው::

- መግቢያ፡- ለምን ቤተክርስቲን እንተክላለን? ይህ ክፍል ቀጥታ ከቤተክርስቲያን ተከላ ጋር የተዛመዱ ሶስት የስነመለኮት ጽንሰ ሃሳቦችን ያወሳል፤ እነርሱም፡- የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መምጣት፣ የእግዚአብሔር ተልዕኮ እና የእግዚአብሔር መንግስት ናቸው::
- ምዘና፡- ስልጠናው ሲጠናቀቅ ተማሪዎች የምዘናውን ፎርሞች ሙሉ በሙሉ ሞልተው እንዲመልሱ ይጠየቃሉ::

የተሳትፎ የምስክውር ወረቀት፡- እነዚህ ክፍሎች በአስተማሪው መመሪያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡

- **አጠቃላይ መመሪያዎች** ተጨማሪ መረጃ እና የቀረቡ መስመጃዎች
- ማውጫ
- የሚመከር የመርሃ ግብር ይዘት፤ በተሳታፊዎቹ ማኑዋል ውስጥ ተግባሮቹ የተዘረዘሩት የጊዜ ገደብን ሳያካትቱ ነው፡፡
- **ተጨማሪ መግለጫ**
  - የመከታተያ ቅፅ፡- እያንዳንዱ ተሳታፊ የማመልከቻ ቅፅ መሙላት ግዴታው ነው፡፡

1. ቦታ

- ቦታው በቂ የሆነ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተሳታፊዎችን በሙሉ የሚያስቀምጥ እና የሚቀርበው ተንቀሳቃሽ ምስል እንዲታይ በበቂ ሁኔታ ሲጨልም የሚችል ክፍል መሆን ይኖርበታል፡፡
- በትልልቅ ወረቀት የምታቀርባቸውን ጽሑፎች ለመለጠፍ ግድግዳው የተመቻ ሊሆን ይገባል፡፡
- ቦታው ለተሳታፊዎች ተስማሚ እንዲሆን  ለማረፍና ለመዝናናት የሚችሉበት አካባቢ እና በእረፍት ጊዜም የአትክልት ቦታ፣ መንቀሳቀሻ፣ መቀመጫዎች እና አግዳሚ ወንበሮች ወ.ዘ.ተ… ሊኖሩት ይገባል፡፡
- ቢያንስ ሶስት የኤሌክትሪክ እቃዎችን በአንድ ጊዜ ለመሰካት የሚያስችል በቂ ሀይል ያላቸው ሶኬቶች ሊኖሩ ይገባል፡፡

2. የጊዜ ሰንጠረዥ

- ስልጠናው የሚጀመርበት ሰዓት እደየአስፈላጊነቱ የተለያየ ይሆናል፤ ነገር ግን ተሳታፊዎቹ መስመጃዎቹን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለእያንዳንዱ ትምህርት 1፡30 መመደብ ጠቃሚ ነው፡፡

3. ትምህርቶች

- እያንዳንዱ ትምህርት የሚጀምረው በዛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጠናቀቅ እንዳለበት ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የትምህርት ማብቂያ እንደገና ግቦቹን ማንበብ፤ ትምህርቱ በትክክል መሰጠቱን እርግጠኛ ለመሆን ይጠቅማል፡፡ ተጨማሪ አስተያየቶችን ለማስፈር በእያንዳንዱ ገፅ በስተግራ ክፍት ስፍራ መጠቀም ይቻላል፡፡

4. **አስፈላጊ ግብአቶች**

በቅድሚያ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም እቃዎች እና አቅርቦቶችን ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው፡፡

- ስም የሚጻፍባቸው ባጆች፡- በራትራቱ ለሚሳተፉ ለሁሉም ስማቸውን ተጽፎ

በደረታቸው ላይ እዲያንጠለጥሉ ማድረግ።

- ኮምፒውተር ከፕሮጀክተር ጋር እና ስክሪን ወይም ባዶ ግድግዳ
- ቴሌቪዥን ከ ዲ ቪ ዲ ማጫወቻ ጋር ወይም ቪዲዮ ካሴት ማጫወቻ (ግዴታ አይደለም)

- ተለቅ ያለ የወረቀት(ኤ1) ልናስቀምጥበት ከምንችል ማስደገፊያ(stand) ጋር።
- የድምፅ ማስተላለፊያዎች ወይም ማጉያዎች
- የወረቀት ማጣበቂያ የሚጣበቁ ማስታወሻዎች እና ርካሽ የጋዜጣ ወረቀት
- የድምፅ መሳሪያዎች (የዕረፍት ሰአት መዝሙር ለመጫወት እና ወይም ኢንስትሩመንታል ሙዚቃ ለመጫወት፤ ተሳታፊዎቹ የትግበራ ነጥቦችን በሚሰሩበት ጊዜ የሚከፈት)
- ከረሜላ፣ ሚንት፣ውሃ ወ.ዘ.ተ በጠረጴዘ ላይ ማስቀመጥ

ኮርሱን ማጠናቀቃቸውን የሚገልጽ ሰርተፍኬት

ለተሻለ ውጤት፤ ቦታው ለተሰታፊዎቹ ለማረፍና ለመዝናናት ሚችሉበት አካባቢ እና በእረፍት ጊዜም የአትክልት ቦታ፣ መንቀሳቀሻ፣ መቀመጫዎች እና አግዳሚ ወንበሮች ወ.ዘ.ተ ሊኖሩት ይገባል።

5. ፕሮጀክተር ወይም ኦቨርሔድ ፕሮጀክተር

ከመጀመራችን በፊት ማንኛውም በፕሮጀክተሩ የሚተላለፉ ምስሎች ከኮንፍራንሱ ክፍል ከየኛውም አቅጣጫ በግልፅ መታየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

6. ግምገማዎች

በተሳታፊዎቹ (በሰልጣኞቹ ማኑዋል ውስጥ ምዘና የሚል ፎርም አለ በሬትሬቱ ማብቂያ ምዘናው ተሞልቶ ለሬትሬቱ መሪዎች ሊመለስ ይገባዋል። መሪዎቹ ምዘናውን በማጠቃለል ወደ መልቲፕሊኬሽን ኔትዎክ ሊልኩት ይችላሉ።

www.multiplicationnetwork.org

## ማውጫ


ክለትምህርት 1

ራዕይን መወሰን /መግለፅ ..........................................

ክፍለትምህርት 2

ሰሌት/ቫሊን ግልጥ በማድረግ ማብራራት ..............................

ክፍለትምህር 3

ተልዕኮን መለየት .....................................................

ክፍለትምህር 4

ራስን ለፀሎት እና ለእግዚአብሔር ቃል መስተት ......................

ክለትምህር5

ቡድን ግንባታ .........................................................

ክፍለትምህር 6

ውጤታማ የወንጌል ስርጭት .......................................

ክፍለትምህር7

እስትራቴጂካል ማቀድ ............................................

ክፍለትምህር 8

ውጤታማ ያገልግሎት ዲዛይን ማድረግ .............................

ክፍለትምህር9

ችግሮችን መቋቋም ..............................................

ክፍለትምህር 10

የራስን ቤተሰብ መንከባከብ ........................................

አባሪ (Appendix) ........................................

1. የምንባብ ክፍሎች
2. ስድስቱ የወንጌል ስርጭት ዜዴዎች መስተንግዶ
3. ቤተክርስቲያን የሚተክሉ አገልጋዮች ፕሮፋይል /ገጽታ
4. ቤተክርስቲያን የሚተክሉ አገልጋዮች ፕሮፋይል ABC
5. የአዲሲቱ ቤተክርስቲያን የልደት ማስረጃ

# ክፍል ትምህርት 1

# ራዕይን መተርጎም

**አላማዎች** /objectives
**ተሳታፊዎች / ሠልጣኞች**

- ራዕይን የመግለፅ ጠቃሚነት ይረዳሉ::
- በራዕይና በተልዕኮ መካከል ያለውን ልዩነት ለተውሉ
- የራዕያቸውን መግለጫ በጽሁፍ ያስቀምጣሉ ወይም ቀድም ብሎ የተጻፋውን የራዕይ መግለጫ ይከልሳሉ::

*"ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና አዘነላቸው።" (ማቴ 9:36)*

## ሀ. ትርጉሞች

የራዕይ ትርጉም፤ "የወደፊቱን መመልከት" እና እግዚአብሔር በአንተ/በአንቺ/ ውስጥ ለመስራት የሚፈልገውን ማየት:: የሰው ልጆችን ለመታደግ የዘረጋውን ዘላለማዊ ዕቅድ መፈፀም::

1. ራዕይ የሌሉትን ነገሮች ነገር ግን እውን ሲሆኑ የሚችሉትን ለማየት እግዚአብሔር የሚሰጠው ችሎታ ነው::

2. የቤተክርስቲያን ራዕይ አቅጣጫዋን እና ሁሉንም አገልግሎቷን ይወስነዋል:: ሒደቱ የሚጀምረው ነገሮች ለሳሉበት ሁኔታ አለመርካት ሲሰማህ ነው:: ሁሌም ባለው ነባራዊ ሁኔታ ምቾት ማጣት ለስራ ለለሚያነሳሳ አስፈላጊ ነው::

አንተም በጣም ጥሩና ሊደረስበት የሚችል የወደፊት ተስፋ ይታይሀል::

3. የራዕይ መኖር ደግሞ የእምነት ጉዳይ ነው:: መክንያቱም በተጨባጭ ልታያቸው ለለማትችላቸው ነገሮች የግዲታ መፍትሔ መሰጠት ይኖርሃል:: ያለዕምነት ራዕይ ሊኖር አይችልም፤ ራዕይ ደግሞ ከሌለ ተልዕኮ የለም

4. ራዕይ ጥረት የሚጠይቅና የወደፊቱን አገልግሎት በግልፅ የሚያሳይ ገፅታ ነው::

**አስታውስ፤** መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ በምድር ላለች ቤተክርስቲያን ለትረዳው እንድትችል ሁሉን አቀፍ ሆኖ የተሰጠ ሲሆን፤ ይህን ዓላማውን በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ደረጃ እንዴት ማስፈጸም ይኖርብናል ብለን የምናስቀምጥበት መንገድ ራዕይ ይባላል::

## ጥቂት የራዕይ ገላጭ አርፍተነገር ምሳሌዎች

"የሰላሙ ልዑል ቤተክርስቲያን በስውጥ ላይ ያለችና ህያው ጉባኤ ብዙ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለክርስቶስ የምትደርስ ናት። ይህ የዕምነት ማህበረሰብ እንደ ዛፍ ነው የሚመሰለው። የሚከተሉትም ይኖረታል።"

- በቃሉ ዕውቀት ስር የሰደደ
- ቀጥ ብሎ እንዲቆም እና ጠንካራ እንዲሆን የሚያግዘው ግንዱ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።
- ማህበረሰቡን እና አለሙን ለማገልገል የተንሰራፋ ቅርንጫፍ፤
- የኛን ክርስቲያናዊ መሰጠት ሚያንፀባርቅ ፍሬ

"ይህ ራዕይ የሚሳካው እየጨመረ በሚሔድ አምልኮ፣ በጠንካራ ሰብከት፣ በመፅሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ልዕቀት፣ አገልግሎቶችን በንቃት በመከታተል እና በመንብኘት፣ ታስቦበት በሚደረግ የወንጌል ስርጭት እና በማህበረሰባችን ውስጥ ለሚገኙ ቤተሰቦችና ልጆች ፍላጎት ላይ ያተኮረ ሲሆን ብቻ ነው።" (Prince of Peace Christian Church, Puerto Rico)

ራዕያችን በሁሉም አቅጣጫ የምናድግ ጉባኤ መሆን፣ በአሰራራችን /ታታሪና እየጨመርን የምንሄድ፣ በመንፈስ የተለወጥን፣ በዶክትሪናችን እና በተግባራችን ደግሞ ቈንጤቆስጢያዊ እና ዓለምን በወንጌል መድረስ የምትችል ቤተክርስቲያን መሆን ነው።

(Christian Reformed Church, Puerto Rico)

"ቤተክርስቲያን በእያንንዳንዱ ህብረተሰብ ውስጥ የምትተከለው በሰለጠኑ የቤተክርስቲያን አባላት ሲሆን፤ በተግባር የሚታይ አብሮ የመስራት ክህሎት ያዳበረ እና አብሮ ለመስራትም የሚበረታቱ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።" (Church Planters Institute)

**ለ. ራዕይ በመፅሐፍ ቅዱስ እይታ**

የሚከተሉት ምንባቦች እያንዳንዳቸው በቃሉ ውስጥ የተገለጡትን የእግዚአብሔርን ራዕይ በምሳሌ ያቀርባሉ፡፡

ዘፍጥረት ፡1-3 ፣ 13፡14-18

2ኛ ሳሙ 7፡5 ፣ 8፣ 12-16፡

ሐ. የራዕይ ጠቃሚነት /አስፈላጊነት

1. የማይመቹ ሁኔታዎች ስራውን እንደትተው ባስገደዱህ ጊዜ እንኳን፤ ራዕይ ግን በስራው ላይ እንደገና ለማተኮር ረዳሀል፡፡

2. ሌሎችን ባንተ ዓውድ ምን መስራት እንዳለብህ እንዳይወስኑ ይከለክላል፡፡

3. "ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል" ምሳሌ 29፡18

**አስታውስ**፤ እንደየ ዓውዱ ራዕይ ሊስተካከል እና ሊለወጥ ይችላል፡፡ ታጋሽ ልትሆን ይገባሃል ምክንያቱም ራዕይ ገና እውን አልሆነም፡፡

**መ. የራዕይ እድገት**

1. ራዕይን በጽሁፍ ግለፅ፡- አጭርና ለማስታወስ በማይከብድ ቀላል ሐረጎች ተጠቀም፤ በአእምሮህ በመያዝ ለሌሎች በሚገባቸው ሁኔታ አስተላልፍ/አስረዳ፡፡

2. ትልቅ አስብ! ራዕይ የሚያንቀሳቅስ ኃይል እና ግልፅ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፤ የሚደረስበትና ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡

3. የፈጠራ ችሎታን የምትጠቀም ሁን፤ በአዲስ ወይም በተለየ መንገድ ለማሰብ ነፃ ሁን፡፡

4. ራዕይን ገምግም /ፈትሽ

- ግልጽ ነኝ ወይ?
- ፈታኝ /ጥረት የሚጠይቅ ነው ወይ?
- ወደፊትን በቀድሚያ በእቅድ መልክ የሚያሳይ ነው ወይ?
- ሊደረስበት የሚቻል ነው ወይ?

5. በግልፅነት እና በፀና እምነት ራዕዩን አካፍለው የጋራ ራዕይና በኢየሱስ ክርስቶስ ማዕከል ማድረግ፤ ለቡድኑ መዋሀድ /ምክንያት ይሆናል፡፡

- ሌሎች ከዚህ ራዕይ ጋር ንድነት እንዲችሉ አመቺ ሁኔታ ፍጠርላቸው፡፡
- በተመረጠው ራዕይ ለእውነታው የሚሰሩ ቡን አቋቁም፡፡
- ራእዩ ሰፊ የሆነ፤ መከራን የሚፈቅድ እና ውድቀት ቢያገጥም ማረም የሚችል መሆን አለበት፡፡
- አዲስ እና ንፁ መንገዶችን መቃነት ፤ በሁሉም ዕይታ ራዕዩ ተቀባይነት እንዲኖረው፡፡

**አስታውስ፤** በሚበልጠው የእምነት ማህበረሰብ ተቀባይነቱን ለማረጋገጥ መሪ የግዴታ ራዕዩን ከሌሎች ጋር መከፋፈል ይኖርበታል፡፡

## ሠ. በራዕ እና በተልዕኮ መካከል ያለው ልዩነት

<table>
<tr><th>ራዕይ ገላጭ አርፍተነገር</th><th>የተልዕኮ መገለጫ</th></tr>
<tr><td colspan="2">ትርጉም</td></tr>
<tr><td>በሁለት ወይም በሶስት አርፍተ ነገሮች አንቀጽ የቤተክርስቲያንን ወይም የድርጅትን ትክክለኛ አሰራር / ምንነት አላማውን በሚያከናውንበተ መልኩ ባጭሩ ሲገልፀው ነው፡፡ እንደለሚኔን ኮከብ ነው የሚያገለግለው ቤተክርስቲያን ወደትክክለኛ አቅጣጫ እንድተትንዝ እና ተልእኮዋን እንድትፈጽም ይረዳታል፡፡</td><td>አጭር አንቀፅ ያንተን ቤተክርስቲያን ወይም ድርጅት እንዴት ራዕዩን እንደሚያሳካ የሚነግር ነው፡፡ ለራዕዩ እግሮችና እጆች ይሰተዋል፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="2">ቁልፍ ቃል</td></tr>
<tr><td>ምን</td><td>እንዴት</td></tr>
<tr><td colspan="2">ምሳሌ</td></tr>
<tr><td>ጤናማ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግስት በሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ ትወክላለች ፡፡</td><td>የቤተክርስቲያን መሪዎችን በመሳሪያዎች እና በሚያስፈልጉ ዕቃዎ ለማስታጠቅ እና ጤናማ ቤተክርስቲያንን ለማጠናከር እና ለማብዛት<br>1. መሪዎችን ማሰልጠን<br>ቤተክርስቲያንን ለሚተክሉ ስልጠና መስጠት እንዲችል ብሔራዊ የአሰልጣኞች መረብ ማቋቋም፡፡<ul><li>ብሔራዊ /በሃገር ውስት ላሉ አማኞች ጋር በመስራት</li><li>በየሰፈሩ ያሉን ቤተክርስቲያኖችን ማሰልጠን</li><li>እንደኛ አሰልጠኞችን ማጠናከር</li></ul>2. የሚባዙ ማቴሪያሎችን ማቅረብ<br>በየትኛውም የአለም ስፍራ ከኮምፒውተር ላይ በነፃ የሚወርድ የመማሪያ መጽሐፍ የመልመጃ መፅሐፍ እና የትምህርት ሞጁል ማዘጋጀት፡፡<ul><li>የኮምፒውተር ትስስርን እንደቢሮዎች መጠቀም</li><li>የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችንን ማዳበር</li></ul></td></tr>
</table>

# የትግበራ ነጥቦች

1. እግዚአብሔር ስመክልክል በአገልግሎትህ/በአገልግሎትሽ መስራት ከቻለ ያንተ ቤተክርስቲያን በሚቀጥሉት አስር አመታት ምን ልትመስል ትችላለች ይሁንና ከሰር ያሉትን ሌሎች ጥያቄዎች ስመመለስ ተሳታፊዎች ትቂት ደቂቃዎች እንዲወስዱ ድርግ።

2. ራዕን ባጭሩ መፃፍ

3. ራዕን ከላይ በሴክሽን "መ" በተጻፈው መሰረት ፈትሸው። ራዕህ በሚታይ ሁኔታ ሲገለጽ ይችላል ወይ? ወደፊት የተመነኃውን ያንጸባርቃል ወይ? አስፈላጊ ከሆነ ራዕይን ጻፈው። ግልጽ ቀላልና ወደዋናው ሀሳቡ የሚያተኩር አድርገው።

4. ከሌሎች ተሳታፊዎች ወይም ከሁሉም ቡድን ጋር ራዕይን ስማካፈል ትንሽ ደቂቃዎችን ውሰድ።

# ትምህርት ሁለት

# ዕሴቶችን ማብራራት

*"አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና"* 2ጢሞ 3፡14

ሀ. ትርጉም

1. እሴቶችን በኑሯችን ሲንፀባረቁ የሚገባ ብህርያት መገለጫዎችና ዝንባሌዎች ናቸው።

2. የኛ እሴቶች በተወሰኑ ተግባሮቻችን ይገለጣሉ

3. ዕሴቶች የማይለወጡ የሕይወት ህግ (ቀኖና) አይደሉም

4. ዕሴቶች በጣሉት መሰረት ላይ ቤተክርስቲያን ግቡን መወሰን ትችላለች።

**አስታውስ፤** ተልዕኮ ቤተክርስቲያን የሚተክሉ ሰዎችን እሴቶች ሊቃረን አይችልም። በእርግጥ ተልዕኮ ከእሴቶች ነው የሚወለደው

**ለ. መፅሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች እና ዋና ድርጅታዊ እሴቶች**

መፅሐፍ ቅዱሳዊ እሴቶች የማንደራደርባቸው መርሆቻችን ሲሆኑ እነርሱም ማንነታችንን የሚገልፁና የክርስትና የሕይወት ዘይቤ አኗኗር የሚወስኑ ናቸው።በሁለትና በሶስት ቡድኖች በመሆን የሚከተሉትን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ፅሁፎች ተመልክታችሁ የተጠቀሱትን እሴቶች ተረዷቸው።

ግቦች፡-

ተሳታፊዎቹ የሚከተለውን ይረዳሉ

- ዕሴትን የመተመን ጠቃሚነት መረዳት
- የዕርሱን ወይም የዕርሷን ድርጅት እሴት መለየት
- እንዴት እሴት በተግባር እንደሚተገበር የእሴት ዝርዝር አዘጋጅ እና ተወያዩበት

ዘፀ 3፡7-10

______________________________

ማቴ 18፡10-14

______________________________

ሐዋ 2፡42-47

______________________________

1ኛ ቆሮ 1፡10

______________________________

2ጢሞ 3፡14

______________________________

**የሚቻሉ መልመጃዎች፡-**

ተሳታፊዎች በቤተክርስቲያን ካላባዊ ሁኔታዎች የወንጌል ስብከት መደረግ አለበት በሚል እሴት ሊወያዩ ይችላሉ፡፡

እንዲህ ብለህ ጠይቃቸው "ቤተክርስቲያን በእርግጥ ለወንጌል ስርጭት ተገቢውን ትኩረት እንደምትሰጥ ለማወቅ ምን አይነት ጥያቄዎች ልትጠይቁ ትችላላችሁ?"

**የሚጠበቁ ምላሾች፡-**

በጀት ተመድቦለታል?

አባሉችን ለማሰልጠን እቅድ ተይዟል?

በወንጌል ስርጭት ዙሪያ መጋቢው ስብከቶችን ያዘጋጃል፤ ያስተምራል?

ከመጽሐፈ ቅዱስ እሴቶች በተጨማሪ ቤተክርስቲያን የሚተክሉ አገልጋዮች ደግሞ የድርጅቱን ዋና እሴቶች ትርጓሜ ሊያስቀምጡ ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ እሴቶች በአንድነት የቤተክርስቲያንን አላማዎች ይወስናሉ፤ ቤተክርስቲያ ያለችበትን አውድም ከግምትውስጥ ያስገባሉ፡፡ "በድርጅቱ የሚከናወኑ ማንኛውም ተግባራት ከዋና እሴቶች ጋር በቀደም ተከተል የተዛመዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስሁሉም ዋና ዋና እሴቶች ድርጅቱ ይህንን አረፍተ ነገር አካትቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል "እኛ በዚህ

እሴት ስር እንደምንተዳደር እናውቃለን...." ብለው መልስ መስጠት ይገባቸዋል።"

"መጽሐፍ ቅዱሳዊ እሴት መልካም ነው። ምክንያቱም ጥልቅ ስሜት ይፈጥራል፣ ከሌሎች ጋር የምትካፈለው ነው፣ ዘወትርም የማይለዋወጥ ነው፣ ነገሮች በግልጥ እንደሚታወቁ የሚያሳይ ነው፣ ከሌሎች እሴቶችም ጋር ስምምነት አለው እንዲሁም በስራ ላይ ልትተገብረው ትችላለህ" ለምሳሌ ያህል የብዜት መረብ አገልግሎት ዋና እሴቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦

- **የክርስቲያን ታማኝነት /ሀቀኝነት/**

እንደ መፅሀፍ ቅዱስ አስተምሮ፣ በደቀመዝሙርነት መንፈስ እና በፀጋው የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች ለመታዝ አላማችን አድርገናል።(ኤፌ 4)

- **የቡድን አመራር**

እኛ የሁሉንም የቡድን አባላት ስጦታዎች እና አስተዋፅኦ በማብዛት፣ በክርስቶስ መንፈስ በመደገፍ ሌሎችን ለማገልገል አላማ አድርገናል። (ፊል 2)

- **ምርጥ የማሰልጠኛ ማቴሪያሎች ዝግጅት እና የላቀ ስልጠና**

መርጥ የስልጠና ማኗሎች ለማዘጋጀትና ደፋዊ ከፍተኛ ትራት ያለው ስልጠና ተብሎ የሚሆን ዝግጅት ለማሰናዳት አላማ አድርገናል። ኤፌ 6፡6-8

- **ሊገባ የሚችልና በቀላሉ የሚገኝ የስልጠና መጽሐፍ**

ለሁሉም ሊጠቀምባቸው ለሚፈልጉ ሊደርስ የሚችል የስልጠና ማቴሪያሎችና ስልጠናዎች በቀላል ልንከተላቸው በምንችለው በዌብ ሳይት ያለማቋረጥ ለማስፋትና መረጃዎችን ለማስፋት አላማ አድርገናል።

- **ታማኝ የግብአት ባለአደራ**

አገልግሎታችን በእግዚአብሔር እና በሌሎች ፊት የጠራ ተጠያቂነት እና ገልፅነት ያለው እንዲሁም የአገልግሎቱን ንብረቶች እና ገንዘቦች መልካም አስተዳዳሪዎች በመሆን አገልግሎት ለመስጠት አላማ አድርገናል።

## ሠ. የዕሴቶች ጠቃሚነት

1. በዙውን ጊዜ ግጭቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከሰቱበት ምክንያት አባላት ከቤተክርስቲያን የተለያዩ <u>የሚጠብቋቸው</u> ነገሮች በመኖሩ ነው፡፡

2. የሚበልጡት የስልታዊ ዕቅድ ጥረቶች የማይሳከበት ምክንያ እሴቶች በሂደቱ <u>ጅማሬ</u> ላይ ያልተብራሩ እንደሆነ ነው፡፡

3. ዕሴቶች በተነገረው እና በተሰራው መካከል ለሚኖረው ግንኙነት <u>ድልድይ</u> ናቸው፡፡ በእምነት እና በባህርይ መሀከልም ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

**አስታውስ፤** ዕሴቶች በቡድኑ ውስጥ በእጅጉ ከተለያዩ፤ መርሃ ግብሩ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ባልተወሰኑ እና በጋራ ስምምነት ባልተደረገባቸው እሴቶች በቤተክርስቲያን አንድነት ሊኖር አይችልም፡፡

## የትግበራ ነጥቦች

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕሴቶች መርህ ዝርዝር አዘጋጅ፡፡ በምን አይነት መልክ ነው እነዚህ እሴቶች ለአዲስ ቤተክርስቲያን የሚቀርቡት? ተሳታፊዎችን ተመሳሳይ እሴቶችን በአንድ ላይ እንዲያስቀምጡ /እንዲያደራጇቸው ጠይቃቸው፡፡

2. ተቀባይነት ያላቸውን የዋና እሴቶችን ዝርዝር አዘጋጅ፡፡ እነዚህ ዕሴቶች የተወሰኑት ድርጊትን እንደሚያንፀባርቁ እርግጠኛ ሁን፡፡

3. ዝርዝሩን በቅደም ተከተል አደራጇቸው፡፡ እያንዳንዱ እሴት በተጨባጭ የባህርይ ምሳሌ ግለፃቸው፡፡ ከሰባት ያልበለጡ እሴቶችን ተሳታፊዎችን እንዲጽፉ ጠይቃቸው፡፡

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

መ. ______________________________

ረ. ______________________________

ሰ. ______________________________

ሸ. ______________________________

# ትምህርት ሶስት

# ተልዕኮን ለይቶ ማወቅ

*"እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ  እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፡፡"*

*ማቴ 28፡19*

**ሀ. ትርጉም /ፍቺ/**

"ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ድርጅትህ እንዴት ራዕዩን እንደሚያሳካ የሚነግርህ ነው፡፡ ለራዕዩህም "እግር እና እጅ" ሆኖ ያንቀሳቅሰዋል፡፡"

Renée N. Hale, MissioDei Partners

ተልዕኮ ከራዕ ጋር ተመሳሳዩ ኤደለም፡፡ ተልዕኮ ቤተክርስቲያን ያላትን ራዕዩ እውን እንዴት እንደምታደርግ መንገድ ነው የሚያሳያት፡፡

## ለ.   ዝርዝር ጉዳዩች

የተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ሶስት ትያቄዎችን መመለስ ደኖርበታል፡፡

### 3. ማንን ነው እያገለገልክ ያለኸው?

ለታገለግላቸው ያሰብካቸው ሰዎች የሚከተሉትን መለያ ባሕርያት

ከግምት ውስጥ ለታስገባ

ያስፈልግሃል፡-

- ዕድሜ
- የገቢ መጠን
- የቤተሰብ ብዛት
- ጎሳና ብሔረሰብ

ግቦች፡-

ተሳታፊዎች የሚከተሉትን....

- ተልዕኮን የመተርጎምጥቅምን ደረዳሉ
- በራዕዩና በተልእኮ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃሉ
- የተልዕኮን መግለጫ መፃፍ ወይም የነበረውን ራዕዩ መግለጫ ደከልሳሉ

**ለመሪዎች ተጨማሪ መረጃ፡-**
ይህ የጥናት ሞዴል የሚያገለግለው ቡድን ፍላጎታቸውን በተሻለ ለመረዳት ልንተቀምበት እንችላለን።

- አንተ የአካባቢህ ቤተክርስቲያን ቋሚ አባል ነህ ወይ?
- በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የበለተው ፍላጎት ብለህ የምታምነው ምንድን ነው?
- አብዛኛው ህዝብ ወደ ቤተክርስቲያን የማይሔደው ለምንድንነው ብለህ ታስባለህ?
- በአካባቢህ ወደቤተክርስቲያን ለመሄድ ብትፈልግ ምን አይነት ነገሮች ነው እንዲሟላልህ የምትፈልገው?
- እንደአካባቢ ቤተክርስቲያን መጋቢ ምን አይነት ምክር ልትለግሰን ትችላለህ?
- ላንተ ምን እንዳደርግልህ ትወዳለህ?
  - ስለእኛ ቤተክርስቲያን የበለጠ መረጃ ለማግኘት ትፈልጋለህ ወይ?

**የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ልዩ ነው፡-**
ሁለት ቤተክርስቲያኖች ተመሳሳይ የተልዕኮ መግለጫ ሊኖራቸው አይችሉም። ምክንያቱም ለሶስቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መልሳቸው የተለያየ ነው የሚሆነው። ይም ሁለት ወይም ከዛ በላይ ቤተክርስቲያኖች በማህበረሰቡ እንዲኖሩ ይፈቅዳል። እያንዳንዱ የተሌዩ አገልግሎት ይኖራቸዋል። የተለያዩ ሕዝቦችን ይደርሳሉ። የተለያዩ ፍላጎቶችን ያረካሉ።

- የትምህርት ዝግጅት ደረጃ
- መደበኛ ሙያቸው
- ቤተሰብና የማህበረሰብ ቡድን
- በትርፍ ጊዜያቸው መስራት የሚወዱት እና

በምታጠናው ሕዝብ መካከል ያሉትን የተለያዩ ቡድኖች በማህበረሰብ ያላቸው ተሳትፎዎች ከመቶ ስንት እጅ እንደሆነ (ፐርሰንት) ከግምት ውስጥ አስገባ።

- ያላገቡ፣ ያገቡ፣ ባል ወይንም ሚስት ሳይኖራ ልጅ የሚያሳድጉ፣ ባል/ሚስት የሞቱባቸውው፣ የተፋቱ
- ባለትዳሮች ሁለቱም ከቤት ውጭ የሚሰሩ ወይስ አንድ የትዳር አጋር ብቻ የሚሰራ ነው።
- የራሳቸው መኖሪያ ቤት አላቸው ወይስ ተከራዮች ናቸው

**2. መሟላት ያለባቸው ፍላጎቶች ምንድን ናቸው?**

ይህ ጥያቄ ሌች ጥያቄዎች ሊከተሉት ይገባል።

* አንተ ለሕዝቡ ለማድረስ የምትፈልገው መልካም የምስራች ምንድን ነው?

* ምን አይነት ፍላጎቶችን ነው ያንተ ቤተክርስቲያን ብቻ ልታሟላ የምትችለው?

**3. እንዴት ነው አንተ ተልዕኮውን ልትፈፅም የምትችለው?**

ይህን ጥያቄ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማካተት መልስ

* የምታገለግለውን ቡድን ለመሳብ ስልቶችን መቀየስ

* የምታገለግላቸውን ቡድን ፍላጎቶች ለሟላት የአገልግሎት አይነቶችን መለየት

* ደቀመዛሙርቶችን እንደምትንከባከብና እንዴት እንደሚበዙ ግለፅ እናም መቼ እንደምትጀምር ግለጽ፡፡

**የተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር ምሳሌዎች**

"የቪዳ ክርስቲያን ተልእኮ ስፓኒሽኛ ተናጋሪ አካባቢ ያሉን የክርስቶስ አካሎች በትንቢታዊ አመራር ለማገልገል ሲሆን ተያያዥ ትምህርቶችና በአለም አቀፍ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራውን ዜናዎች ለማብሰር በአለም አቀፍ ህብረተሰብ ዘንድ ድልድዮችን ገንቢዎች እንድንሆን እኛን ለመርዳት ነው፡፡"

(ካሪዝማ በተሰኛ መጽሔት ላይ ከታተመ አንድ ማስታወቂያ ላይ የተገኘ)

"የኛ እስፓኒክ አገልግሎት የሚኖረው የእስፓኒክ ቤተክርስቲያናትን ለማስታጠቅ፣ የጠፋትን ለመፈለግ፤ አዲስ ደቀመዛሙርቶችን ለማፍራት፤ እና በትውልድ ለማዘጋጀት ነው፡፡"

(Christian Reformed Church of North America)

""የእኛ" ቤተክርስቲያን የምትኖረው በታኮማ ዋሽንግተን አካባቢ ሲሆን የእስፓንክ ቤተሰቦችን በመንፈሳዊ፣ ስሜታዊ፤ አሰምሯዊ እና አካላዊ ልማት የሚጠናከርበትን ከባቢ በማጠናከር ለመንፈሳዊ እድገት ማብቃት ነው፡፡"

(The Rock Church, Open Bible Church)

**መ. መፅሐፍ ቅዱስና የቤተክርስቲያን ተልዕኮ**

በነዚህ ቤተክርስቲያን በተቋቋመችበት ዓላማ በሚገልጥ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ላይ ያለህን ሃሳብ ግለፅ፡፡

ሉቀስ 24፡46-48

________________________________________

________________________________________

ሐዋ 2፡42-47

________________________________________

________________________________________

ገላ 6፡10

**መሪዎች**

ተሳታፊዎችን ይህንን መልመጃ በጥንድ ወይም በቡድን እንዲሞሉት ጠይቃቸው

ኤፌ 4፡3-4

1ኛ ዮሐ 2፡3-6

1ኛ ዮሐ 4፡7-12

**መ. ተልዐኮ ገላጭ አርፍተነገር ለምን አስፈላጊ ሆነ?**

1. የቤተክርስቲያን ተልዕኮ በግልፅ ባይብራራ ምን ሊደርስ ይችላል?

- የ<u>ትኩረት</u> ጉድለት ሊታይ ይችላል
- ምን መስራት ባለብን ነገር ላይ የማያቋርጥ ግራመጋባት ይሆናል፡፡
- ቤተክርስቲያን ወደ ራዕዩዋ ባለመጓዟ <u>ግራ መጋባት</u> ይሆናል
- የአመራር ቡድን አባሎች መሀከል የበለጠ <u>አለመግባባቶች</u> ይሆናሉ፡፡

2. ከተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገር የሚገኙ ጥቅሞች

- ተግባሮች በግልጽ ከራዕዩና ከግብ ጋር <u>የተያያዙ</u> ናቸው
- መሪዎች ምን አይነት ፍላጎቶች መከናወን እንዳለባቸው ያውቃሉ እና ጊዜያቸውን በማያስፈልጉ ተግባሮች ላይ <u>አያባክኑም</u>፡፡
- የትኞቹን ፍላጎቶች መከናወን አለባቸው በሚሉ ጉዳች መሪዎች በተደጋጋሚ አይከራከሩም፡፡
- ወደ ራዕዩ የማያመሩ ተግባሮች <u>ሊወገዱ</u> ይችላሉ፡፡

**ለ. የተልዕኮ እና ራዕይ ገላጭ አርፍተነገሮችን መጠቀም**

1. የተልዕኮ እና ራዕይ ገላጭ አርፍተነገሮችን አጥንተህ **በቃልህ ያዛቸው** እንዲሁም የቡድን አባሎችህ እንደዚሁ እንዲያደርጉ አበረታታቸው።

2. አርፍተነገሮቹን **በፍሬም** ውስጥ አስገብተህ በቢሮህ፣ በቤትህ እና በቤተክርስቲያንህ ግድግዳ ላይ አኑራቸው።

3. በቤተክርስቲያን የዕለት ተዕለት መመሪያህ ውስጥ **አካታቸው**

4. በሁሉም የአገልግሎት ቡድን አባላት ውስጥ እስኪቀረፅ ድረስ **ደጋግመህ** አርፍተነገሮቹን አንብብ።

5. በትክክለኛ መስመር ላይ መሆንህን እርግጠኛ እንድትሆን በቋሚነት **ራስህን ገምግም**።

# የትግበራ ነጥቦች

1."ለምንድነው ይች ቤተክርስቲያን እዚህ የተተከለችው?" ለዚህ ጥያቄ በአንድ አረፍተ ነገር መልስ ፃፍ

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

2. ተልዕኮ ገላጭ አርፍተነገርህን የሚከተሉትን አሳች በዝርዝር በማካተት ጻፍ ሀ.) ማንን ነው በወንጌል ለመድረስ የምትመኘው? ለ.) (በእግዚአብሔር ባርኮት) ራዕዩን እውን ለማድረግ ያንተ በተክርስቲያን የምታከናውናቸው ተግባሮች ምንድን ናቸው?

3. የሚከተሉትን ያያቄዎች በመጠየቅ ያንተን የተሰፅኦ መግለጫ ገምግም

ሀ. ተሰፅኦህ ያንተን የአገለግሎትህን አላማ ቡድን ይስየዋል ወይ?፤ አላማ የደረግከው ቡድበን አንተ ቀድመህ ከሰየኸው በእርግጥ ስለቡድኑ የምታውቀውን ለመፈተሽ ይህ ድንቅ ጊዜ ነው።

ለ. ያንተ አግልግሎት ለማሟላት ያላቸውን ፈላጎት ተሰፅኦው ያብራራል ወይ?

መ. መፅሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር ይስማማል ወይ? ዘላቂ ነው ወይ?  አጠር ያስ ነው ወይ? በአዕምሮ ሊያዝ ይችላል ወይ?

(አስፈላጊ ከሆነ ከላይ ያሉትን መመዘኛዎች ባሟላ ሁኔታ የተሰፅኦውን መግለጫ ፃፈው)

4. የተሰእኦ መግለጫን በአምስት ወይም በአስር ቃላቶች የሚጠቀለል መፈክር አበልጽግ።

5. የተሰፅኦ መግለጫዎችን ለማስተላለፍ አያሌ መንገዶችን ዘርዝር

# ክፍለትምህርተ 4

# ራስን ለጸሎት እና የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት መስጠት

*"ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ፣ በዚያም ጊዜ ስለእርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ሚስጥር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ፀልዩ፡፡" ቆላ 4፡2-3*

*"ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጽሐፍትን አውቀሀል፡፡ እግዚአብሔር ሰው ፍፁምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት እና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ሁሉ ይጠቅማል፡፡"2ጢሞ3፡15-17*

**የእግዚአብሔር እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል**

ፍቃዱ በቃሉ አማካኝነት እንዲታወቅ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር መነጋገርን መረጠ፡፡

- ከእግዚአብሔር ጋር የራሳችንን ግንኙነት እና ከክርስቶስ አካል ጋር ያለንን ግንኙነቶች ለማጠናከር ፀሎት በጣም አስፈላጊ ልምምድ ነው፡፡ ከሁሉም አስቀድሞ በፀሎት ለእግዚአብሔር ራሳችንን እናቀርባለን፡፡ ደግሞ እርሱን እንሰማለን፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ክርስቲያኖች አብረው በሚፀልዩበት ጊዜ በመሀከላቸው ያለው ህብረታቸው የተበቀ ይሆናል፡፡

"ፀሎት ለጦርነት መዘጋጀት አይደለም፤ ፀሎት ጦርነት ነው፡፡"

"መፅሐፍ ቅዱ ለዚህ ጦርነት ራሳቸውን ማዘጋጀት ለሚፈልጉ የቀረበ ምግብ ነው፡፡
...ሰዎች የራሳቸውን ጽድቅ ለመጠበቅ የሚከውኑት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በፀሎት ትግል ውስጥ ለተሰማሩት በአለም በእምነት ጦርነት ውስጥ ላሉት ሁሉ ነው፡፡

የመፅሐቅ ቅዱስ ጥናት በመጨረሻው በራሱ እየደበዘዘ ይሄዳል። ነገር ግን በማንኛውም ውጊያ ውስጥ ሳሉት የሚዋሀድ አልሚ ምግብ ያስፈልጋቸዋል። የበላነው የምግብ ብዛት ሳይሆን ያገኘነው የመፅሐፍ ቅዱስ ዕውቀት የምግቡን ብዛት ሳይሆ፤ ነገር ግን ይልቁንም የተዋሀደው መጠን ነው የሚጠቅመን።"

ግቦች

ተሳታፊዎ ... ያደርጋሉ...

አሁን ያላቸውን የፀሎትና የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ልምምዶች ገለጽ

## ሀ. ቤተክርስቲያን የሚተክል አገልጋይ ግዴታዎች

1.ለዋናው ቡድን መንፈሳዊ ብልፅግና ራስህን አሳልፈህ ስጥ

- ፀሎትና የመፅሐፍ ቅዱስ ንባብ የእያንዳንዱ አባል የሕይወታቸው ዋናው ጉዳይ እንደሆነ አረጋግጥ።
- እያንዳንዱ አባል በየቀኑ የግዴታ ክርስቲያን ሳልሆኑ ሰዎች መፀለይ እንዳለባቸው አጽንኦት ስጠው።

2. ለመፅሐፍ ቅዱስ ስልጠና ቡድንህ አነቃቃቸው።

ሀ. የመፅሐፍ ቅዱስ ኮርሶችን በመደበኛ  ወይም ራስ በማጥናት ዘዴ ቀጣይነት ሳለው ስልተና ምሳሌ ሁን።

ለ. ያንተ ዋናው ቡድን በመፅሐፍ ቅዱስ ስልጠናው በንቃት እንዲሳተፉ መንገድ ፈልግ።

- ስለ ስልጠና ያለውን አመቺ አጋጣሚዎች ንገራቸው
- ለስልጠና የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ አቅርብ።
- ለስምን ማጥናት እንዳለባቸው ጊዜ ወስደህ ንገራቸው።

3. <u>የማሳጆች</u> ቡድን አሰባስብ

ሀ. ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ዝርዝር ፃፍና የናንተን የአማሳጆች ቡድን እንዲቀሳቀሱ ጋብዛቸው። ሚስጥር መጠበበቅ፤ የእርስ በአርስ

በቡድን የመፀለይ መንገዶች በተመለከተ የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርበናል።

- ከጊዜ በኋላ የተሴ ፍላጎታቸውን በመጠየቅ አባሎች በቀኝ ወይም በግራ ሳለው ሰው እንዲፀልዩ አበረታታቸው። እንዲህ በማድረግ እያንዳንዱን ሰው ለሌላው ሰው መፀለይ ቻለ ማለት ነው።
- የተለየ ፍላጎት ያለውን በግል እንዲፀለይለት በክቡ መሀከል አቁመው እናም ሌሎቹ ለእሱ/ለእሷ እንዲፀልዩ አድርግ።
- ከ5 እስከ 10 ቂቃዎች ፀሎት ለመፃፍ ጊዜ ውሰድ። ከዛም በኋላ ደግሞ የፃፍከውን አንብበው።
- በፀሎትና በምልጃ ወቅት ሰዎች የፀጥታውን ሰዐት ራሳቸውን እንዲያዩበት ምስጋናን ለእግዚአብሔር በማቅረብ እንዲጠቀሙበት አበረታታቸው።

ግንኙነት እና ከእነርሱ ስለሚጠበቅባቸው ጉዳዬችን በሚመለከቱ ርዕሶች ላይ ትምህርት መስጠት እንዳትረሳ።

ሰ. ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ለአማሳጆች ቡድን መፀለይ አለበት።

ሠ. እነርሱን ለማበረታታት የፀሎት መልሶችንና ልዩ ፍላጎቶችን ለመጋራት እንዲሁም በብቃት የሚፀልዩ እንደሆነ እና አንተ የግዴታ ሴሎችን ማግነት ካለብህ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በአካለ መገናኘት ያስፈልጋል።

## 4. ፀሎትን ዋና ማድረግ

1. ለአዲሷ ቤተክርስቲን የፀሎት <u>ምሳሌዎች</u> ማቅረብ

• በቤተክርስቲያን አገልግሎት ወቅት፤ ፀሎት ሁሉም የሚረዳው በጊዜው ቃላት መጠቀም እና በእምነት የተሞላ መሆን አለበት።

• ከሰዎችጋር እድል በተገኘ ጊዜ ሁል ፀልዩ። በእያንዳንዱ ደቀመዝሙር የትምህርት ጊዜ ወይም በማማከር የአገልግሎት ጊዜ ጭምር፤ ይህም ያስማቋረጥ ለመፀለይ አንዱ መንገድ ነው።

• ስትጸልዩ ደግሞ ድምፅህን የሚሰማ፣ ግልፅና አጠር ያለ እንዲሁም ሊየሱስን ማከል ያደረገ መሆን ይኖርበታል።

2. ሁልጊዜ ለፀሎት <u>መልሶችህ</u> ምስጋና አቅርብ። እግዚእብሔር ለፀሎቶችህ ምላሽ ሲሰጥ ከማየት በስጠ የሚያበረታታ መንም ነገር የለም። በዐል ስታደርግ ከልብህ በምስጋናና በትህትና ይሁን።

**አስታውስ፤** አንድ ትክክለኛ የሆነ የመፀለይ መንገድ የለም። ስትፀልዩ በመንፈስ ይሁን ደግሞ ቀስ ብለህ መፀለይ እንዳለብህ አስታውስ። በጥንቃቄ ቃላቶችህን ምረጥ እናም የምትለው ሁሉ በማስተዋል ይሁን። ይህም የእግዚአብሔርን ስሞች በጸሎት ጊዜ አንደምርኩዝ እንድትጠቀም ይረዳሀል። የበለጠ የንግግር አይነት ፀሎት እንድታደርግ ይፈቅድልሀል።

ለ. የፀሎት እና የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ውጤቶች የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና ለምንፀልይበት እና የእርሱን ቃል ለናጠና እግዚአንሔር የሚያደርገውን ነገር ለዩ።

ኢያሱ 1:8

መዝ 40:1-3

መዝ 119:105

ማቴ 4:3-4

ማቴ 7:7-11

ፊል 1:9-11

# የትግበራ ነጥቦች

1. ዋና የመፅሐፍ ቅዱስ እሴቶችን ዝርዝር አዘጋጅ፡፡ በምን አይነት መንገድ ነው እነዚህን እሴቶች ለአዲስ ቤተክርስቲያን የሚቀርቡት? ተመሳሳይ እሴቶችን በአንድ ላይ እንዲያደራጇቸው ተሳታፊዎቹን ጠይቃቸው፡፡

2. ተቀባይነት ያላቸውን ዋና እሴቶች ዝርዝር አዘጋጅ እነዚህን እሴቶች የተወሰነ ድርጊት እንደሚያሳዩህ እርግጠኛ ሁን፡፡

3. ዝርዝሩን በቅደም ተከተል አደራጃቸው፡፡ እያንዳንዱ እሴት ተጨባጭ በሆነ ድርጊታዊ ምሳሌዎች ግለፃቸው፡፡ ተሳታፊዎቹን ለባት የሚሆኑ እሴቶችን እንዲፅፉ ጠይቃቸው፡፡

ሀ.

ለ.

ሐ.

ሠ.

ረ.

ሰ.

ሸ

# ክፍለትምህርት 5

# ቡድን መገንባት

*"ሁልጊዜ በፀሎቴ ሁሉ በደስታ እየፀለይሁ÷ ከፊተኛው ቀን እስከዛሬ ድረስ ወንጌልን በመስበክ ስለተባበራችሁኝ አመሰግናችኋለሁ" ፊል ቁር 1:4-5*

*"አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት አይደለምና፡፡" 1ኛ ቁር 12:14*

## ሀ. ቡድን የመገንባት ጠቀሜታ

የሰው ልጅ የሰውነት ሴሎች ይፈጠራሉ ወይም ይሞታሉ፡፡ በተመሳሳይ መንገድን በክርስቶስ ቤተክርስቲያ ደቀመዛሙርቱን ካላፈራችሁ እናም ሌሎችን በአገልግሎት ውስጥ ካላተፋችሁ ቤተክርስቲያ ማደግ አትችልም፡፡

በተክርስቲያን ለመጀመር የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ስራዎች ፓስተር ብቻውን ሊሰራው አይችልም፡፡ ሁሉን በራስ ለመስራት መሞከር ባንተ በኩል ወደድካም ሊያመራህ በሌሎች በኩል ደግሞ የፀጋ ስጦታዎችን ባለመጠቃማቸው ወደተስፋ መቁረጥ የሔዳሉ፡፡

ራዕይህን ከወሰንክ በኋላ ተልዕኮህን ግለፅ ዕሴቶችህን ደግሞ አብራራ፡፡ የሚቀጥለው እርምጃ ቤተክርስቲያን ለማቋቋም ዋናውን ቡድን ማሰልጠን ይሆናል፡፡ (በአንዳንድ ሁኔታዎች ዋናው ቡድን አንድ ቤተክርስቲያን ተቶ በመሄድ ሌላ ቤተክርስቲያን ይጀምራል፡፡ ስለዚህ ዋናው ቡድን በራዕይ፣ በተልዕኮና በእሴቶች ላይ አብሮ መስራት ይችላል፡፡)

ከአንተ ጋር ተቀላቅለው አዲ ቤተክርስቲያን እንዲጀምሩ ለመመልመልና ሰዎችን ለማሰልጠን አያሌ መንገዶች አሉ፡፡ ያለምን ጥርጥር ወንጌልተሰበከላቸው ሰዎች ከፊሉ ደቀመዛሙርት እና የቀረት የዋናው የአመራር ቡድን አባል ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም ሌሎችን ያንተ ዋና ቡድን አባሎች እንዲሆኑ ልትመለምላቸው ትችላለህ፡፡ ከዚያም አዲሲቱን ቤተክርስቲያ ትገነባለህ፡፡

## ለ. ቡድንን ለመምረጥ ምርጥ ልምምዶች

1. <u>ራዕይ</u>፣ <u>ተልዕኮ</u> እና <u>ዕሴቶች</u> ከተወሰኑ እና በፅሁፍ ከተቀመጡ በቡድኑ ውስጥ ያሉት ሰዎች ያሉት ሰዎች ነገሩ እንደገባቸው እና እንደተስማሙ እርግጠኛ ሁን፡፡ ውሳኔዎች በእነርሱ በሀሳባቸው እየተፈፀሙ እንደሆነ እናም ወደራዕይህ እየገሰገስክ እንደሆነ እርግጠኛ ለመሆን ራዕይ ተልዕኮንና እሴቶችን ሁልጊዜ ከልሳቸው፡፡
2. አገልግሎቱን እንደቡድን <u>አካፍላቸው</u> አብረህም መፀለይ እና ለተለያዩ የአገልግሎት ተግባሮች ስልቶችን ተወያዩ፡፡ (አዳዲስ ክርስቲያኖችን መከታተል፤ ክርስቲን ካሆኑ ሰዎች ጋር መገናኘት የመሳሰሉትን…)
3. በቡድኑ ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱን ሰዎች የፀጋ ስጦታዎችን <u>  ለይ  </u>፡፡ ብርታቸውን እና ማደግ የሚያስፈልጋቸውን አቅጣጫ ላይ ለአባላት ስጦታቸውን በሚመጥን መልኩ ተግባሮችን ደልድል፡፡
4. ያንተን ቡድን አባሎች ወደሚጨምር <u>የኃላፊነት</u> ደረጃዎች መድባቸው፡፡ ይህ የወደፊቱን ተግባሮች ለመውሰድ ያዘጋጃቸዋል፡፡
5. ሳታቋርጥ ቡድንህን <u>አበረታታ</u>፤ በሚያስፈልጋቸውም ጊዜ እጅህን ዘርጋላቸው፡፡ በግልም በጉባኤም መካከል ምስጋና አድናቆት ስጣቸው፡፡
6. በጋራና በግል ቡድንህን <u>አሰልጥናቸው</u>፡፡ ቤተክርስቲያን ሲጀመር መሪዎችን ለማሰልጠን ጊዜ መመደብ ለቤተክርስቲን ስኬት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉንም ባብድ ሳይሆን በአንድ ጊዜ አንዱን ለመቅረፍ ድካሞቻቸው ላይ እንዲሰሩ የቡድኑን አባሎች እርዳቸው፡፡
7. የትዳር ጓደኛህን/ጓደኛሽን የአዲሱ በተክርስቲያን ደጋፊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ እናም የሱን/የሷን የፀጋ ስጦታዎች መጠቀም  ቤተክርስቲያኗን ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ሆኖም ግን እኛ ያንተ/የአንቺ የትዳር ጓደኛ የአመራሩ አካሉ አባልነትን አናበረታታም፡፡ይህም

ግቦች፡-

ተሰታፊዎች..

- በቡድን የመስራትን ጠቀሜታ ይረዳሉ
- ምርጥ የሚባለውን የመሪነት ተግባርን ይረዳሉ
- የቀደመውን የቡድን አመራር ልምዳቸው ላይ ያላቸውን አሳብ ማንጸባረቅ እና በቀጣይ ቡድን በመገንባቱ ረገድ የሚጠበቅባቸው እርምጃ ምን እንደሆነ ይገነዘባሉ፡፡

በአገልግሎት እና በትዳር ሕይወትህ መካከል ጤናማ ወሰኖች ስመከለል ይረዳሀል፡፡ በጥቂት አውዶች ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

8. መወያየት፣ መወያየት፣ መወያየት ከሞላው ቡድን ጋር እናም ደግሞ ከሁሉም አባላት ጋር አንድ ለአንድ ለመነጋገር ጊዜ ውሰድ፡፡ ጉዳይ ወይም ፍላጎት ካጋጠመ አንተ የምትገኝላቸው መሆንህን የቡድን አባላቱ ይወቁ፡፡

## መ. ችግሮችን መፍታ

1. ሰዎችን የቡድኑ አባል እንዲሆኑ ስትጠይቃቸው በጊዜው ሲሆኑ አስመቻላቸውን ቢገልፁም፤ ማስተዋል ያስብህ በገር "አልችልም" ማስታቸው "ለጊዜው አይመችኝም" ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
2. አስቸጋሪ ውሳኔ በሚገጥምህ ጊዜ በመጀመሪያ ቡድኑ በጋራ <u>እንዲጸልይ</u> አድርግ ከዛ ውሳኔው በአእምሯችን ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶችን ባረጋጠ መልኩ ተደርጎ እንደሆነ ፈትሸው፡፡
3. ግጭቶች ወዲያውኑ እንደታዩ <u>መፍትሔ</u> ስጣቸው፡: ሰዎች ራሳቸውን እንዲገልፁ እድል ስጣቸው፡፡ እናም እርስ በርሳቸው በጥንቃቄ እንደሚደማመጡ እርግጠኛ ሁን፡፡ ጥሩ መደማመጥ ሞዴል ይሁን፡፡
4. ልታደርገው የማትችለውን ነገር ቃል አትግባ፡፡ አደርጋለሁ ብለህ ቃል የገባኸውን ነገር ብለህ ነገር ግን ልታደርገው ካልቻልክለስተናገርከው ነገር ታማኝ ሆነህ ወዲያውኑ ይቅርታ ጠይቅ፡፡

## ሠ. የስኬታማ ቡድኖች ስምንት ባሕርያ

ስኬታማ ቡድን የሚከተሉት ይኖሯታል፡-

1. ግልጽና የሚያነሳሱ <u>ግቦች</u> ይኖራቸዋል፡- ሁሉም በደንብ ስታወቀ ግብ ለመድረስ ሲሰሩ የቡድኑ ጉልበት ይጨምራል፡፡ የቡድኑ የጋራ አላማቸው ይጠናከራል፡፡

2. ውጤቶች ላይ ለመድረስ የሚረዳ **መዋቅር** ይኖረዋል፡፡ ቡድኑ ስኬት ለማግኘት በተመቻቸ መንገድ ነው መደራጀት ያለበት፡፡
3. **ብቁ የሆኑ** የቡድን አባሎች፤ አሸናፊ ቡድን ኃላፊነታቸውን እና ስራቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች ይኖሩታል፡፡
4. በቡድኑ አባላት ዘንድ መስጠትን **የመጋራት** ባህል መኖር፡- የቡድኑ አባላት አንዳንድ ጊዜ ለቡድኑ መልካም እንዲሆን ሲባል የግል ምርጫን የግዴታ መስዋዕት መክፈል እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡
5. **ተባባሪ የሆነ** ከባቢ፡- የስራ አካባቢ ጥሩ ግንኙነትና የመተባበር ፍላጎትን የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡
6. **የልዕቀት** መለኪያ፡- ጠንካራና ውጤታማ ቡድኖች እንደነገሩ ወይም መሀከለኛ በሆነ ውጤት አይረኩም፡፡ የሚያልሙት በራሳቸው እጅግ የላቀ ውጤት ማስመዝገብን ነው፡፡
7. የውጭ ድጋፍና **እውቅና** ማግኘት፡- ቡድኖች ድጋፍ የሚቸሩ እና ከሌሎች ማረጋጫ የሚያገኙ የተሸለ ግባቸውን ለመምታት ወደፊት ያመራሉ፡፡
8. **መርህን** መሰረት ያደረገ አመራር፡- መሪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጋራ በተስማሙበት መርሆች ላይ የተመሰረቱ ከሆነ በራስ መተማመን ያዳብራሉ፡፡ ቡድኑም በተሸለ ይሰራል፡፡ እናም ግቦቻቸውን ይፈፅማሉ፡፡

## የትግበራ ነጥብ

በአንድ ቡድን ሶስት ወይም አራት ሰዎች ሆናችሁ የሚከተሉትን ስሩ፡-

1. ለስኬታማ የቡድን ስራ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ዘርዝሯቸው፡፡

2. በአገልግሎትህ የገጠመህን አንድ ምሳሌ ስጥ....

- ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ሌሎችን ያሳተፍክበትን
- በአገልግሎት ውስጥ የሱን/የሷን የጸጋ ስጦታዎች እንዲጠቀሙበት እድል የሰጠህበትን
- በግጭት ውስጥ መስራት እንዲችሉ ሰዎችን የረዳህበትን
- ቡድኑን በመልካም ባለመምራትህ ያጋጠመህ ነገር ካለ?

3. የአመራ ቡድኑን ለማብቃት መውሰድ የምትፈልገው ሁለት ቀጣ እርምጃዎች ምንድን ናቸው?

ሀ.

ለ.

# ክፍለትምህርት 6

# ውጤታማ በሆነ መልኩ ወንጌልን ማሰራጨት

*“የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ” ሐዋ 8፡4*

## ሀ. ወንጌል ለመስበክ ቃል መግባት

የመጨረሻው ክርስቶስ ወደሰማይ ከማረጉ በፊት የሰጠን ትእዛዝ፡- “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው፡፡

ማቴ 28፡19” ማንኛውም ቤተክርስቲያን መጀመሪያ ቅድሚያ ወይም ቅድሚያ የምትሰጠው ነገር መሆን አለበት፡፡ ደቀመዛሙርቶችን በማፍራት ሂደት፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው አንድ ሰው ይተክል ሌላው ውሃ ያጠጣል ነገር ግን እግዚአብሔር ነገሮችን ያሳድጋቸዋል፡፡ 1ቆሮ 3፡6-7 ይህ ነገር ዛሬም እንደዚሁ ነው እየተከሰተ ያለው፡፡ የመጀመሪያውን የወንጌል ምስክርነት አንደኛው ሰው ያቀርባል፤ አንደኛው ደግሞ ተጨማሪ ማብራሪያ እና መልሶች በመስጠት ይከተለዋል ነገር ግን ዋነኛው የሆነው ልባቸውን በመቀየር ሕዝቡን ወደራሱ ቤተሰብነት በመጨመር ይቀጥላል፡፡ ቤተክርስቲያን አሁንም እግዚአብሔር የጠፉትን ለማግኘትና ደቀመዝሙር ለማድረግ የሚጠቀምባት መሳሪያ ነች፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ለተመረጡት እንዲህ ይላል፡- ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን፡፡ ኤፌ 1፡4 የተመረጡት እነማን እንደሆኑ ስለማናቅ ለአለም ሁሉ የየምስራቹን ቃል እናውጃለን፡፡ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት እንደሚሰራ ስለምናውቅ፤ አዎንታዊ ምላሽ ለወንጌል እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡ እኛ እየሔድን በአለም ሁሉ ደቀመዛሙርቶች ስለምናደርግ በዚህም ሂደት እኛ የእግዚአብሔር መሳሪዎች ነን፡፡

እግዚአብሔር በስራ ላይ ስለሆነ ቤተክርስቲያኖች እድገት ሲጠብቁ ችላሉ፡፡ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን እንደአዳኝ ወደማወቅ ይመጣሉ እናም እርሱን በመታዘዝ ይኖራሉ፡፡ ብዙ ቤተክርስቲያኖች ግምታቸው በጣም ዝቅተኛ የሆነ እና ሁልጊዜ የተሳካላቸው መኖራቸው ይህ በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ እነሱ በቀላሉ ምንም አላደጉም፡፡

## ለ. ወንጌልን ለመስበክ ቁልፍ መርሆች፡-

- ውጣና የጠፉትን ፈልግ፡፡ (እነርሱ ወደአንተ እስኪመጡ አትጠብቅ)
- እግዚአብሔር ዋና ለሚሰጠው ዋጋ ስጡ፡፡
- አንተ ስትደርሳቸው የምትሞክረውን አመለካከታቸውን ተረዳቸው፡፡
- መንፈሳዊ ነገር ለሚያስፈልጋቸው ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
- መልዕክቶችን ሳይሆን ዘዴዎችን አዳብር፡፡
- መልዕክቱን ለማስረፅ የተመቻቸ ሁኔታ ፈልግ (በመንፈስ ቅዱስ የተዘጋጁ ሰዎችን ፈልግ)
- ትርጉም በሚሰጡ መንገዶች ወንጌል በግልፅ ይነገራቸው፡፡
- በብዙ አሳ ማጥመጃዎች አሳ መያዝ ወንጌልን በብዙ መንገዶች ከብዙ ሰዎች ጋር መካፈል፡- በቃሎች፣ በተግባሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች ወ.ዘ.ተ መካፈል፡፡
- ወንጌል ስርጭት በፀሎት ማገዝ
- ውሳኔዎችን ሳይሆን ደቀመዛሙርቶችን ፈልግ፡፡
- ባሉትና በተለመደው ግንኙነት ውስጥ ስራ፡፡

ግቦች
ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ይረዳሉ
- በውጤታማነት ወንጌልን ለመስበክ ቁልፍ መርሆች ይማራሉ፡፡
- ልዩ ወንጌል የሚሰበክላቸውን ሰዎች እና እንዴት በወንጌል እንደሚደርሳቸው መንገዶቹን ያስረዳል፡፡
- የራሳቸውን በግል የተመረጡ የወንጌል ስርጭት ዘዴዎችን ይለያሉ፡፡

## ሐ. ወንጌል የምትሰብክላቸው ሰዎች ላይ አተኩር

የተወሰነ የሰዎችን ቡድን ወንጌል በመስበክ ለመድረስ አተኩር ይህ መፅሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ነው፡፡ እናም ደግ ተግባራዊ ነው፡፡ ልክ አምላክ ስጋ እንደለበሰ በኢየሱ አካ ከሰው ልጆች ጋር

አንድ እንደሆነ እናም በቤተክርስቲያን(የክርስቶስ አካል) ኢየሱስ በተለያዩ ህብረተሰብ ውስጥ ስጋ ለበሰ፤ ከፋላጎቶቹ ጋር አንድ አድርጎ አጠቃላይ ወንጌልን አመጣልን፡፡

አንዳንድ ሰዎች የተወሰነ ቡድን ላይ የማተኮርን ሀሳብ ይቃወማሉ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው ጴጥሮስና ጳውሎስ እንደዚሁ አድርገዋል፡፡ አንደኛው ለአይሁድ እና ሌላኛው ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ ተጠርተዋል፡፡ ነገር ግን ወንጌልን ለመስበክ ተጠርተዋል፡፡ ነገር ግን ወንጌልን በሰበኩበት ጊዜ ማንንም አላገለገሉም፡፡ እነሱ የተወሰኑ ቡድኖችን ለመድረስ ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ እውነት ነው፡፡

በግል የተመረጡ የትኩረት ቡድኖች መኖር፤ ውሳኔዎችን ለመስጠትና አገልግሎቱን ለመፈፀም ቀላል ያደርገዋል፡፡

ወደተለዕኮ መግለጫ ተመለስና በትምህርት ሶስት ላይ (ገፅ 19) ም አይነት ቡድኖች ነው በወንጌል ለመድረስ የፈለግከው?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

ወንጌል ከእነርሱ ጋር ለመካፈል ምን አይነት የበለጠ ውጤታማ መንገዶች (ዘዴዎች) ይኖራሉ?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

ለነኚህ ሰዎች ቡድኖች ለመስበክ ከወሰንካቸው አንዳንድ መንገዶች ምናልባት ውጤታማ የሚያደርግህ የትኞቹ ናቸው?

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

## መ. ወንጌልን ለመስበክ ማቀድ

አዲስ ቤተክርስቲያን ለሚተክሉ ዋናው ስራቸው በተለይም ደግሞ በመጀመሪያ ወንጌልን መስበክ የግድ ይሆናል፡፡ ጠንካራ ቤተክርስቲያኖች ወንጌል መስበክን ሆን ብለው ነው የሚያደርጉት፡፡ እናም ትኩረታቸውን በሚካሔደው በወንጌል ስርጭት ፕሮግራቃም ያካትቱታል፡፡
ለወንጌል ስርጭት ቀድሚያ እንዲሰጠው የእቅዱ አካል እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ለወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴዎች ማከናወኛ የበጀት መስመር መኖሩን እርግጠኛ ሁን፡፡ እናም በአጀንዳው ላይ መርሃ ግብር መያዝ ይኖርበታል፡፡ ወንጌልን ከሕዝብ ጋር መካፈል አልፎ አልፎ የሚከሰት ጉዳይ ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡

## ለ. የግል የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች

አዲስ ቤተክርስቲያኖችን በመትከል ዐውድ ውስጥ ሆነን ስለወንጌል ስርጭት ስንወያይ ሰዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያነሳሉ፡፡ “ወንጌልን ለማድረስ የተሻለ መንገድ የትኛው ነው? የተሻሉ ውጤቶች እንዴት እንፈጥራለን? ምን አይነት ዘዴዎችን እንጠቀም?”

እውነቱ ሁሉም የኛን የወንጌል ስርጭቶችን ተግዳሮቶች ሊፈታልን የሚችል ምትሀታዊ ቀመር የለም፡፡ አዲስ ቤተክርስቲን ለሚጀምሩ ተስማሚ ዘዴዎች የግድ መፈለግና ወደተግባር መግባት ይኖርባቸዋል፡፡
በወንጌል ስርጭት ዘዴዎች ላይ የሚከተሉትን ጥናት እንድትወስድ አሳብ እናቀርባለን፡፡ እና ባንተ የአመራር ቡድን ያሉትን ሰዎ ጥናቱን እንዲያደርጉ አበረታቸው፡፡ በአንተ ጉባችኤ፤ ባንተ ቡድን የተመረጡ የወንጌል ስርጭት ሰዎች ጋር የተሻለ ለስራ የሚመቸውን አቀራረባችሁን የሚመጥኑ መንገዶችን ፈልግ፡፡

ማስታወሻ ጊዜ ከፈቀደና የወርክሾፕ / የስልጠናው መሪዎች እንድናደርግ ከነገሩን ነጥብ “መ” ተጨማሪ መረጃ ወንጌል ስርጭትን እናነባለን፡፡

# የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች ጥናት

ዚህ በታች የቀረቡትን 36 መዘርዝሮች በማበብ እኔን ይገልጠኛል የምትለውን ነጥብ ከአንድ እስከ አራት በቁጥር የቀረበውን መግለጫ ተጠቀም፡፡

1. ምንም 2. በጣም ትንሽ 3. በቂ 4. ብዙ

1. ውይይትን በተመለከተ፡- ብዙ ሳላመራ ወይም ትንሽ ንግግር ሳላደርግ ርዕሶችን በቀጥታ ማቅረብ እወዳለሁ፡፡
2. መፅሐፍት መሸጫ ወይም ከመፅሐፍት ቤት ገብቼ ማህበረሰቡ የሚከራከርብቸውን ርዕሶች እንዳውቅ የሚረዱኝን ክምር መፅሐፎች ካልሰበሰብኩ መውጣት በጣም እቸገራለሁ፡፡
3. ብዙውን ጊዜ የግል ልምምዶቼን ታሪኮች በማካፈል አንድን ነጥብ ለበማብራራት መልዕክቴን ለማስተላፍ እጥራለሁ፡፡
4. እኔ ማለት ሰዎችን የምወድ ሰው ነኝ፡፡ እኔ ለጓደኝነት በጣም ብዙ ዋጋ ነው የምሰጠው፡፡
5. እኔ በምሳተፍበት አገልግሎት ውስጥ አዲስ ሰዎን ማካተት ወይም መጨመር ያስደስተኛል፡፡
6. ሌሎች ብዙውን ጊዜ የሚያዩትን እኔ በሌሎች ሰዎች ሕይወት ፍላጎቶችን አያለሁ፡፡
7. አስፈላጊ ከሆነ ሰዎችን በቦታው ለማስቀመጥ አልፈራም፡፡
8. ነገሮችን መመርመር እወዳለሁ፡፡
9. ብዙውን ጊዜ ራሴን ከሌሎች ሰዎድ ጋር አመሳስላለሁ የሚከተሉትን ነገሮችን የሚመስልበመጠቀም "እኔል ተመሳሳይ ነገር ነው የማስበው ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚሰማኝ፡፡"
10. ሌሎች ሰዎች አዲስ ጓደኞችን የማፍራት ችሎታ እዳለኝ አስተያየት ሰጥተውኛል፡፡
11. እውነቱን ለመናገር መልሶቹን ባውቅ እንኳን ሌላ ሰው ከኔ የበለጠና ብቁ የሆነ ክርስትናን ለጓደኞቼ ሲያስረዳቸው እኔ በጣም ይመቸኛልል፡
12. የተደረገው ነገር በገሀድ አይሁን እንጂ ሌሎችን መርዳት በጣም እርካታ

ይሰጠኛልል፡

13. ምንም እንኳ ግንኙነታችንን አደጋ ላይ የሚጥል ቢሆን ጓደኞቹን ስለእውነት ለመጋፈጥ ምንም ችግር የለብኝም።

14. በመንፈሳዊ እድገታቸው ለሰዎ እድገት ማግኘት ወይም ማጣትን በተመለከተ ውይይት ላይ በጣም ትኩረት አደርጋለሁ።

15. እንዴት ክርስቲያ እንደሆንኩኝ ለሰዎች ለነግራቸው ፍላጎት እንዳደረባቸው ተረድቻለሁ።

16. ስለ ስነመለኮት ፅንሰ ሐሳቦችን ይልቅ እኔ የግለሰብ ጉዳዮችን ነው መወያየት የምመርጠው

17. ታላቅ የወንጌል ስርጭት ዝግጅት እንዳለ ካወቅኩ የኔ ጓደኞች የሚደሰቱበት ስለሆነ እነርሱን ለመጋበዝ ሁሉንም ጥረት አደርጋለሁ።

18. እኔ ብዙ ቃላቶቼ ይልቅ በተግባሮቼ ፍቅሬን ማሳየት እነርጣለሁ።

19. ምንም እንኳ ቢጎዳም እውነተኛ ፍቅር ብዙ ጊዜ ለሌላ እውነቱን መናገር ማለት እንደሆነ እኔ አምናለሁ።

20. እኔ አስቸጋሪ ጥያቄዎችን መወያየትና መመካከር እወዳለሁ።

21. ስህተቶቼን ከሌሎ ጋር እጋራለሁ በተለይም እኔ ካገኘኋቸው መፍትሔዎች ጋር የሚዛመድ እና እነርሱን የሚረዳቸው ከሆነ።

22. እኔ ለሰዎች እምነታቸው ዝርዝር ጉዳዮችን ከመነጋገራችን በፊት ለሕይወታቸው የሚደረገው ውይይት መሳተፍ እመርጣለሁ።

23. የኔ አዝማያ ሰዎችን ልዩ የወንጌል ስርጭት፤ የመዝሙር፣ የራ ግብዣ፣ የስብከት ዘመቻ የመሳሰሉት ሲደረጉ አጥብቆ መጋበዝን ነው የማስበው።

24. ሰዎች ለመንፈሳዊ ነገር ዝግ ሲሆኑ በፀጥታ የማሳያቸው የክርስቲያን ፍቅር አንዳንዴ የበለጠ ተቀባይ ያደርገዋል።

25. እኔን የሚገልፀኝ ለኔ ማበረታቻ ማለት÷ የሚጠቅም ነገር መስራት፤ አደጋ እንኳ ቢኖርም ነገር ግን አንድ ነገር ማድረግ ነው።

26. እኔ ብዙ ጊዜ በሰዎች ተስፋ የምቀርጠው ደካማ ክርክርና የማይሰራ ሎጂክ ሲጠቀሙ ነው።

27. ሰዎች ምን በሕይወቴ እንዳለፈ ታሪኬን ለመስማት ፍላጎት ያላቸው ይመስላሉ።

28. ከጓደኞቼ ጋር መነጋገር ያስደስተኛል፡

29. እኔ ሁልጊዜ የጓደኞቼን ፍላጎታቸውን እና ፍላጎታቸውን ከተለያዩ ዝግጅቶች ወይም መፅሐፍቶች ጥቅም ሲያገኙ ወይም ሲደሰቱ ከሚችሉባቸው ጋር ለማገናኘት ጥረት አደርጋለሁ።

30. እኔ በሃይማኖት ውይይቶች ከመሳተፍ ይልቅ ሰውን በክርስቶስ ስም መርዳትን እመርጣለሁ።

31. ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት የምጠቀምበት መንገድ ስሜታዊ ስለምሆንና ብልሃት ስለሚጎድለኝ አንዳንዴ በችግር ውስጥ እወድቃለሁ።

32. እኔ ለሌሎች ሰዎች ያላቸውን አስተያየቶች ምክንያታቸውን መስማትና መረዳት እወዳለሁ።

33. እግዚአብሔር ወደርሱ ስቦ በእርሱ እንደአምባ እና እምነቴን ለሌሎች እንዳካፍለው ያበረታታኝን መንገድ እስካሁን አደንቃለሁ።

34. ባጠቃላይ ሰዎች ተግባቢ የሰዎችን ስሜት የምረዳ እና ሰው ወዳድ እንደሆንኩ ያስባሉ።

35. በሳምንቱ ውስጥ የሚያስደንቀኝ ነገር እንግዳ ወደቤተክርስቲያን ልዩ ዝግጅት ይዞ መሆድ ነው።

36. በፍልስፍና ሃሳቦች ከመመራት ይልቅ የኔ አዝማሚያ ይበልጥ ተግባራዊና ተግባር መርህ መሆን ነው።

የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች

| ተግዳሮት | የአእምሮ | ምስክርነት | ግለሰባዊ | ግብዣ | አገልግሎት ተኮር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | 32 | 33 | 34 | 35 | 36 |
| ድምር | | | | | |

## የወንጌል ስርጭት ስልቶች

1. ተግዳሮት፡- ርዕሱ በመፀሐፍ ቅዱስ÷ 2ጢሞ 4፡2 የመፅሐፍ ቅዱስ ምሳሌ ጴጥሮስ፤ ሐዋ 2፡14-23
2. የዐዕምሮ፡- ርዕሱ በመፅሐፍ ቅዱስ፡- 2ኛ ቆሮ 10፡5 የመፅሐፍ ቅዱ ምሳሌ ዕውር ሆኖ የተወለደው፤ ዩሐ 9፡10-15
3. ምስክርነት ፡- ርዕሱ በመፅሐፍ ቅዱስ÷ 1ኛ ዩሐ 1፡1-4 የመፅኸፍ ቅዱስ ምሳሌ ማቴ፤ ሉቃ 5፡27-29
4. ግለሰባዊ፡- ርዕሱ በመፕሐፍ ቅዱስ÷ 1ኛ ቆሮ 9፡22 የመፅሐፍ ቅዱስ ምሳሌ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴትዮ፤ ዩሐ 4፡28-30
5. አገልግሎት ተኮር፡- ርዕሱ በመፅሐፍ ቅዱስ÷ ማቴ 5፡16 የመፅሐፍ ቅዱስ ምሳሌ ዶርቃ፤ ሐዋ 9፡33-36

# ክፍለትምህርት 7

# ስልታዊ እቅድ

“ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በስርአት ይሁን፡፡” 1ኛ ቆሮ 14፡40

## ሀ. ስልታዊ እቅድ ምንድን ነው?

ስልታዊ እቅድ እንደዚህ ሊፈታ ይችላል፡- “አባሎች አንድን ድርጅት የወደፊታቸውን ተስፋ በማድረግ የሚመራበትአሰራሮችን እና ቀደምተከተሎችን በመሳደግ ወደፊት ለማድረስ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡እደዚህም ደግሞ ሊፈታ ይችላል፡- መጨረሻውን በአእምሮ ይዞ በመጀመር እና አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ያንን መጨረሻ ማከናወን ነው፡፡”

አንዳንድ መሪዎች እቅድ መንፈሳዊ አይደለም ብለው ያምናሉ ምክንያቱም በመንፈስ እንዳይመሩ እንደሚከለክላቸው ያስባሉ፡፡ እነርሱ እንደዚህ ይላሉ፡- ስልታዊ እቅድ ለአሉታዊ ለሆነው እግዚአብሔር ወይም ድንገታዊ አሰራር ሳለው ለመንፈሱ ቦታ አይሰጠውም፡፡ ነገር ግን እኛ ለእግዚብሔር አሳፌነት አለብን እንደመንፈሳዊ እንደመልካም መጋቢነት በኛ ስር ሳስቀመጠው ንብረቶች እና እቅድ በዚህ በመጋቢነታችን ጠቃሚ ሚና ይተገብራል፡፡ በምንወስደው ውሳኔዎች እግዚአብሔር እኛን እንደመራን እየጠየቀን ሁልጊዜ ከፃሎት ጋር እቅድ ማቀናጀት ግዴታ ነው፡፡

## ለ. ዕቅድ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ቅድመ ምሳሌዎች አሉት

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዕቅድ ብዙ ምሳሌዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል በዘፍ 41፤ እግዚአብሔር ለፈርዖን ሰባት የጥጋብ አመታት ተከታትለውም ሰባት የድርቅ አመታት እንደሚኖሩ ገልፃለት ነበር፡፡ ይህም ፈርዖን ሕይወትን ለማትረፍ ቀድሞ እቅድ እንዲያደርግ አስችሎታል፡፡ በዘፀ 18 ዩትሮ ለሰዎች የመፍረድ ስራን እውቅና በመስጠት ሙሴን ረድቶታል፡፡ ሙሴ (እስራኤልን ለመምረጥ)

ግብ፡-

ተሳታፊዎች የሚከተለውን ያደርጋሉ..

- ዕቅድ የማድረግ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን መከለ
- ቤተክርስቲያን ለመትከል መሰረታዊ እርምጃዎችን መማር
- ለአዲሲቷቤተክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት ለመክፈል ዕቅድ ማዘጋጀት

ትክክለኛ ግብ ነበረው ነገር ግን ሁሉን ስራ ራሱ ብቻውን ነበር የሚሰራው፡፡ ከግብረገብ አኳያ ስህተት አልነበረም የተሳሳተ ዘዴ በመጠቀሙ ምክንያት እጅግ ደከመ፡፡ አማቹ ግን ተግባራዊ መፍትሔ ሰጠው በሺዎች በመቶዎች በሃምሳ እና አስር ላይ ፈፊራጆችን እንዲሾምላቸው መከረው፡፡ ሙሴ ያን አደረገ፡፡ እናም እግዚአብሔር ህዝቡን ባረካቸው፡፡ (ዘጸ 18ን አንብቡ)

እቅድን በተመለከተ የምሳሌ መፅሐፍ አያሌ ምንባቦች አሉት፡፡

- "… መልካምን <u>የሚያቅዱ</u> ፍቅርንና ታማኝነትን ያገኛሉ፡፡" (ምሳሌ 14፡22)
- ምክር ከሌሎች ዘንድ የታሰበው <u>ሳይሳካ</u> ይቀራል÷ መካሪዎች በበዙበት ዘንድ ግን ይፀናል፡፡ ምሳሌ 15፡22
- ስራህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ <u>አሳብህም</u> ትፀናለች ምሳሌ 16፡3
- የሰው ልብ መንገዱን <u>ያዘጋጃል</u> እግዚአብሔር ግን አካሔዱን ያቀናለታል፡፡

የነህምያ መፅሐፍ እንዴት ነህምያ የእየሩሳሌምን ቅጥር መልሶ ግንባታውን እደመራ ይነግረናል፡፡ ለምሳሌ እሱ ከመሄዱ በፊት ወደኢየሩሳሌም ለጉዞው እና ለከተማዋ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በቅድሚያ አሳስቧቸዋል፡፡ ነሕ 2፡7-8

የመልካም እቅድ ጠቃሚነት ሕንፃ ስለመገንባት እና ስለርነት ስለመዘጋጀት አጥብቆ ነግሮናል፡፡ ይህ ከዚህ በኋላ ሰሰዎች ተጠቅሞበታል፡፡ እሱን እንደሚከተሉ ለሚያስቡት የሱ ደቀመዛሙርቶች ከመሆናቸው በፊት ዋጋቸውን እንዲተምኑ መክሯቸዋል፡፡

በቡድን እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉ አዲስ ቤተክርስቲያ አገልሎት ለመክፈት ግብ አድርገው የቆሙ ተሳታፊዎች እንደሚኖረ እናሳስባለን፡፡ ሂደቱን ከተከተሉ በኋላ እቅዳቸውን ቡድኖቹ ይከፋፍላሉ፡፡ ደንን ለማድረግ ወረቀቶች ቴፕና ማርከሮች ያስፈልጎችኋል፡፡

## ሐ. የእቅድ አዘገጃጀት ሞዴል

### 1. ሂደቱ

ሀ. መሪው  እያንዳንዱ ቡድን ለዚህ መልመጃ የሚሆነውን ግብ ይሰጣቸዋል፡፡ በቡድንህሀ ውስጥ ግብህን ለመድረስ የሚካተቱ የአካበቢውን ነገሮች ዝርዝር አዘጋጅ፡፡

ለ. አንድ ወረቀት በመጠቀም የአካባቢውን ነገሮች ከአካባቢው ጋር የተያያዙ ከ5 እስከ 10 ተግባሮች ፃፍ

ሐ. ሀሳቦቹን በጥቁር ሰሌዳ ወይም በግድግዳ ላይ ቅደም ተከተል ባለው ተከታታይ ለጥፋቸው፡፡ ተያያዥነት ባላቸው ተግባሮች ውስጥ በመሙላት የበለጡ ሃሳቦችን ለመጨመር አዲስ ገፃችን ተጠቀም

መ. ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠውን አካባቢ ለያቸው

ሠ. ሃሳቦችን በቅደም ተከተል ስርዐት አደራጃቸው እያንዳንዱን ተግባር ለማጠናቀቅ በቂ የሆነ ጊዜ መመደቡመን አረጋግጥ

ረ. አስታራኦች (ኦከቦችን ሊወክሉ የሚችሉ ተግባሮች አጠገብ አስቀምጥ፡፡ ለእያንዳንዱ ተግባር ሃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር መዝግብ)

ሰ. የሚያስፈልጉትን ተጨማሪ አቅርቦቶች ወስን በጀት ጥሬ እቃዎች ንብረቶች ወ ዘ ተ

## 2. የዚህ አሰራር ጠቀሜታው ወይም ብልጫው

ሀ. አንድ ቡድን ወይም በግል መስራት መቻሉ

ለ. ዝርዝሮች ውስጥ ሳትገባ በአጠቃላይ ዕቅድ ላይ ለመስራት ይፈቅድልሀል፡፡

መ. ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልግህ መለየት እንድትችል ይረዳሃል፡፡

ሠ. በቀላሉ ወረቀቶቹን በዙርያ በማሽከርከር የተግባሮችን ቅደምተከተል ለመለወጥ ይፈቅድልሃል፡፡

ረ. እቅዱን በምታከናውንበት ጊዜ ዕድገቱን ለመቆጣጠር እንዲረዳህ የተግባሮቹን ዝርዝር ወደ ዝርዝር መቆጣጠሪያ መቀየር ትችላለህ፡፡

## መ. አዲስ ለሚከተሉ ቤተክርስቲያኖች እቅድ የማድረግ መርሆች

5 ክህሎት እና እውቀት አንድ ሰውቤተክርስቲያኖች እንዴት እንዴት እንደሚተክሉ ብዙ ሊያውቅ ይችላል ነገር ግን ዋናው ጉዳይ እሱ ወይም እሷ ይህንን እውቀት ወደተግባር

ሊያውሉት ይችላሉ ወደ ነው፡፡ አደማንኛም ሙያ ቤተክርስቲያንን ለመጀመር ቀጣይ ልምድ ይጠይቃል፡፡

6. **በአእምሮ ከመጨረሻው መጀመር፡፡** አዲስ ቤተክርስቲን ለመጀመር እርምጃዎችን ስታከናውን ሁልጊዜ የግዴታ የመጨረሻ ግብ በአእምሮህ ይኑርህ፡፡ ሁሉም እርምጃዎች አንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰሩ ናቸው፡፡ እናም ዲዛይን የሆኑት አዲ ቤተክርስቲያን ወደመንግስት የሚጨመሩ ናቸው፡፡

7. **"ልክ በጊዜው" ስልጠና፡-** ስለቤተክርስቲያን አጀማመር ስራውን በእርግጥ መስራት እስክትጀምር አንተ ሁሊንም ለማወቅ የምትፈልገውን ማወቅ አይጠበቅብህም፡፡ ከዛም እያንዳንዱን እርምጃዎች ስራላይ ለማዋል እና እንዴት እንደሚሰራ ትክክለኛ መቼ እንደሆነ ልትወስን ትችላለህ፡፡

8. **በዓውዱ የሚሰራውን ተለማመድና ደጋግመው፤** ደህና የሚሰራ ጥቂት ነገር ካገኘህ ተመሳሳይ ነገር ማድረግን ቀጥል፡፡ ለምሳሌ፡- ወንጌል በራስህ ዓውድ ለማቅረብ ውጤታማ መንገድ ካገኘህ አንተ የሚሰራ አዲስ መንገዶች እስኪመጡ ድረስ መጠየቅ የለብህም፡፡

9. **እድገትህን ለካ፤** ስራው የግድ በሆነ መንገድ በሆነ መንገድ መሳካት አለበት ስለዚህ አንተ የምታደርገውን ውጤታማና ፍሬያማ እንደሆነና እንዳልሆነ ማወቅ ትችላለህ፡፡ አንተ የአዲስ ግንኙነቶችን ቁጥር እና እንዴት አንተ እነርሱን እንደምታገኛቸው የሰዎች ቁጥር ወደ አምልኮ አገልግሎቶች የሚመጡትን ወዘተ መለካት ትችላለህ፡፡

10. **“ዝግጁ፣ እሳት፣ ዓላማ”** በጣም ጠቃሚው ነገር መስራት መቻል ነው፡፡ ከዛ አንተ ለእቅድህ ማስተካያዎችን በቀጣይነት ማድረግ ትችላለህ፡፡ ሁሉም ያንተን ጊዜ በመነጋገር እና በማቀድና ባለማከናወን አታባክን፡፡

11. **የቃሉ ማዕከላዊነት**

አዲስ ቤተክርስቲን ለመጀመር የምትወስዳቸው ሁሉም እርምጃዎች የግዴታ ፍፁም በሆነ መንገድ አዲስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ወደጠበቀ ግንኙነት በማሳደግ ይመራቸዋል፡፡

ህብረቱ ግንኙነቱ የሚመጣው በመስማት÷ በማንበብ÷በማጥናት የእግዚአብሔርን ቃል በመቀበል ነው። (ማር 4፡1-20)

## ለ. አዲ ቤተክርስቲን ለመጀመር መሰረታዊ እርምጃዎች

1. **አዳዲስ ግንኙነቶችን መፍጠር፡-** አዲስ ግንኙነቶችን ለመፍጠር መጠቀም የምንችላቸው ብዙ ዘዴዎች አሉ። ቤተክርስቲያንን የሚተክል ሰው የግድ ማወቅ ያለበት

ለምሳሌ፡-

ከሰዎች ጋር ግንኙነቶችን ለመፍጠር ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን እንዲያጋሩ ጠይቃቸው። እያንዳንዱን ተሳታፊዎች ለእነርሱ

- የት እና እንዴት አዲስ ሰዎችን መተዋወቅ እንዳለበት
- እንዴት ውይይት እንደጀምር
- አዲሱን ሰው ወደክርስቶስ ህብረትና ወደቃሉ እንዴት እንደሚመራቸው

ምርጥ ዘዴዎች የረጅም ጊዜ ግንኙነቶችን ለማሳደግ ዕቅድ የሚሰጡት ናቸው። ሁሉም ቤተክርስቲን የሚተክል ወንጌልን ለመስበክ ብዙና የተለያዩ መንገዶች ለመሞከር ክፍት መሆን አለበት።አንዳንድ የሚቻሉ ስልቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በህብረተሰቡ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር መነጋር የአገልሎት ፕሮጀክቶች፣ የውጭ አገልግሎቶች፤ ፊልሞች፣ ልዩ የበአል ዝግጅቶች፤ ለተጋቡ ጥንዶች የምሳ ዝግጅት ወዘተ...

2. **አነስተኛ የሰው ቁጥር ያላቸው ቡድኖች የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት መጀመር፤** አዲስ ግንኙነቶችን ከመፍጠር በኂላ አዲስ ቤተክርስቲያን የሚተክለው ሰው የበለጠ እነርሱን ሲያውቃቸው እናም የወንጌል መልእክት የበለጠ በጥልቀት እንዲገባቸው ሲረዳቸው ያስፈልገዋል። ትንሽ ቡድኖች በቀደመችው ቤተክርስቲያ ሕይወት ውስጥ በጣም ጠቃሚ ነበሩ። በሐዋርያት ስራ 20፡20 በቀደመችው ቤተክርስቲያን ብዙ ቡድኖች በቤተመቅደስ እና በትንንሽ ቡድኖች ደግሞ በተለያዩ ሰዎች ቤቶች ውስጥ ሲገናኙ ነው የምናየው ትንሽ ቡድን አዲስ ሰዎችን ደቀመዛሙርት ለማድረግ ምርጥ መንገድ ነው። በተጨማሪ የሚያስተምርና የታወቀ ሲሆን ብዙ ጭነት የሌለውና አዳዲስ

መሪዎች የሚለዩበትና የሚሰለጥኑበት ቦታ ነው፡፡የቡድኑ አባሎች ትንሹን ቡድን ለመምራት የሚያስችል ችሎታ ሊማሩ ይችላሉ፡፡ እናም ወዲያውኑ የራሳቸውን ቡድኖች ይመራሉ፡፡

3. አባል እንዲሆኑ ሰዎችን ማበረታታት ይህ ደረጃ ብዙውን ጊዜ ቤተክርስቲያን የሚተክሉ ሰዎች መካከል የበለጠ የተረሳ ነው፡፡ እንዴት አባሎች የሌሉትን ቤተክርስቲያ ትጥራለህ ይን በአእምሮህ ያዘው፡፡ በቤተክርስቲን አባል መሆን / ራስን መስጠት ኢየሱስን ለመቀበል ከመወሰን የተለየ ነው፡፡ በሕዝብ ፊት በዘላቂ በመስጠት የቤተክርስቲን አባል ከመሆን ይልቅ ወደመሰዊያው ሄዶ ኢየሱስን መቀበል ይህ ለሰዎች በጣም ቀላ ነው፡፡ አባልነት ደግሞ አዲስ መሪዎችን ላማሳደግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ራሳቸው በግልፅ አካል ሆነው ቤተክርስቲያንን ያልተቀላቀሉ ሰዎችን በአመራር ቦታዎች ማስቀመጥ የተለመዱ ስህተት ነው፡፡
4. የአምልኮ አገልግሎት እና ለህብረተሰብ ወንጌል ስርጭት

ዋናው የሰዎች ቡድን እና ለመሰብሰቢያ የሚሆን ቦታ ወዲያውኑ እንደተዘጋጀ አገልሎቶች ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ የትኛውንም ቤተክርስቲያን የመትከል ዘዴ መከተልህ ችግር የለውም፡፡ በጣም ጠቃሚው ነገር አንዴ ማምለክ ከጀመርክ ማቆም የለብህም፡፡

አስታውስ፤ ፅናት ቤተክርስቲን ለሚተክል ሰው መለያው ነው፡፡ በአምልኮ አንተ በህዝብ ፊት የክርስቶስ አካል በዛ ቦታ መገኘት ታውጃለህ፡፡ የመጀመሪያውን የአምልኮ አገልግሎት በህብረተሰቡ ዘንድ በተቻለ መጠን በስፋት አቅድ እናም ጊዜውንና ቦታውን ማስታወቂያ ተናገር፡፡

ሀ. ቤተክርስቲያን የሚተክል ሰው ማድረግ ያለበት

ጥናቶችን ከወንጌሎች በአንዱ ላይና አጠቃላይ የመፅሐፍ ቅዱስ ምልከታ መሰረታዊ የመፅሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች /ዶክትሪንስ እና መሰረታዊ የቤተክርስቲያን አስተምሮዎች÷ የሐዋሪት

መግለጫ /እምነት የሚባሉ ክፍሎች ዋና የቤተክርስቲን አስተምርሆች በተመለከተ የላቀ ምልከታ ይሰጣል፡፡

ለ. ደቀመዛሙርትን ለጌታ አዲስ ቃልኪዳን እንዲገቡ መጋዝና የአዲሷ ቤተክርስቲያን አባሎች እንዲሆኑ ማዘጋጀት፡፡

ሐ. ስለጥምቀት ማስተማርና እንዲያጠምቁ ማድረግ

ሠ. ስለጌታ እራት /ቅዱስ ቁርባን ማስተማርና እንዲያደርጉት ማድረግ፡፡

ለትንሽ ቡድኖች መሰረታዊ አቀራረብ

ሀ. "ለመተዋወቅ በሚል" ጥያቄ ወይም ፀጥታውን ለመስበር ግለሰብ ባላተኮረ አንዳንድ ንግግሮች ውይይት መክፈት ትችላህ፡፡

ለ. ብዙ ተሳትፎን ለማበረታታት ጥያቄዎችን በመጠቀም ጥናቱን ትመራለህ፡፡

ሐ. የፀሎት ጥያቄዎችን እና መልሶችን እንዲያካፍሉህ ሰዎችን ጋብዝ፡፡

ሠ. ለጥያቄዎች ፀልይ

መሪዎችን የማሰልጠን ሂደት ይህንን ይመስላ

ሀ. "እኔ አደርገዋለሁ አንተ አስተውል"

ለ. አንተ ከፊሉን አድርግ እኔ እረዳሃለሁ፡፡

ሐ. ሁሉን አንተ አድርገው እኔ እዴት እንደደረሰ ገምግሜ እረዳሀለሁ፡፡

ሠ. እና አንተ ሁለታችንን ሌላ የሚያሰለጥነነን እንፈልጋለን

## አመራርን ማበልፀግ

የሚቀጥለው እርምጃ አመራርን ማበልፀግ ነው፡፡ በአዲሲቷ ቤተክርስቲያ ሁሉም አባሎች ልንጠቀምባቸው የምንችለው መንፈሳዊ ስጦታዎች አሏቸው፡፡ ቁልፉ ነገር እነዚህ ስጦታዎች ምን እንደሆኑ መለየት አለባቸው፡፡ አመፈራ ሰው ከወሰናቸው ሹመቶች ይልቅ እግዚአብሔር በውስጣችን የሰጠውን ስጦታዎች ውጤቶች መሆን አለባቸው፡፡ መሪን ለማሰልጠን የተሸለው መንገድ በግል ከእነርሱ ጋር አብሮ በመሆን እና ከእነርሱ እድገት አስተዋፅኦ የሚያስፈልገውን ጊዜ በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ በማበርከት ነው፡፡

## 6 ሕብረተሰቡን ማገልገል

ሕብረተሰቡን ማገልገል አንዱና የተሸለው መንገድ፤ ሰዎቹ አንተ ማን እንደሆንክ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ እናም አንተ በሰፈረ የኢየሱስ እጆችና እግሮች እንደሆንክ ያያሉ፡፡ እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ግድ ይለዋል፡፡ እናም የራሱን ቤተክርስቲን ራዕዮች አካባዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲያሟሉ ነው የጠራት (ራዕ 2፡14-16)፡፡ ሕብረተሰቦች ክርስቲኖችን በተግባር ሲመለከታቸው ሰዎችን ስለኢየሱስ ለማሰማት የበለጠ ክፍት ይሆናሉ፡፡

# የትግበራ ዕቅድ

በሚቀጥሉት ሶስት ወሮች ውስ ምን መሰራት እንዳሰበት ወስን/ኚ።

1. እንዴት አዲ ግንኙነቶች ታደርጋለህ?

2. በትንሽ ቡድን፤ በህዋስ ቡድን እ በመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ማንን ነው እንዲሳተፉ ልትጋብዝ የምትችለው?

   ምን አይነት ጥናት ነው ልታደርግ ያሰብከው?

3. የአዲሷ ቤተክርስቲያን ቋሚ አባል ስለመሆን ለመማር መጋበዝ ዝግጁ የሆነው ማን ነው?

   አንተ አባልነት ማለት ም እንደሆነ፤ ለእነርሱ እንዴት ነው የምታብራራው/ሪው?

4. አንተ ለመሪነት ማንን ነው ልታሰለጥናቸው የሚገባቸው? እና አንተ እንዴት ነው እነሱን የምታሰለጥናቸው?

5. ለአምልኮ አገልግሎትና ለህብረተሰቡ አገልግሎቶች የአንተ እቅዶች ምንድን ናቸው?

# ክፍለትምህርት 8

# ውጤታማ አገልግሎት ማቀድ

*“ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ፀጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደመሆናችሁ እያንዳንዳችሁ የደጋ ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዛው ፀጋ እርስረ በእርሳችሁ አገልግሉ" 1ኛ ጴጥ 4:10*

ጤናማ ቤተክርስቲያን በተፈጥሮዋ በመንፈስ ቅዱ ትመራለች። አዲስ አማኞችን በቤተክርስተፊን ውስጥ እንደምትዋሀድ ታውቃለች። አዲ ሰዎን በፍቅር በመቀበልና ስጦታዎቻቸውን በአገልግሎት እንዲጠቀሙ ለእነርሱ መንገዶችን ታመቻቻለች በዚህ መንገድ አዲስ አማኞች ያድጋሉ። የዘመናዊነት ስሜት፤ አሳማም ይኖራቸዋል። ይህ የትምህርት ክፍል በመጀመሪያ ቤተክርስቲያንን አንድ አንድ ስርአት ለመርዳት ይረዳታል። እና በመቀጠል ሰዎችን እንዲሻገሩ/ወደፊት እንዲራመዱ የሚያስችል ሂደት ዲዛይን በማድረግ ከአነስተኛ ደረጃ ግንኙነቶች፤ በቤተክርስቲያን ውስጥ ወደላቀ በአገልግሎት ውስጥ ወደመሰማራት ደረጃ ያመጣቸዋል።

## ሀ. ቤተክርስቲያን እንደ ሲስታም/ስርአት

በስነጥበብ /በሳይንስና በህክምና የሰው ሰውነት ከአያሌ ንዑስ ሲተሞች የተሰራ አንድ አካ መሆኑን ሰዎች ተገንዝበውታል፦ የደም ዑደት ሲስተም÷ የነርቭ ሲስተም÷ የአንገት ሲስተም÷ የምግብ መፈጨት ሲስተም÷ የመተንፈሻ አካ ሲስተም ወዘተ ናቸው። እነዚህ ንዑስ ሲሰተሞች አንዱ በሌላው የሚረዳዱና የተሳሰሩ ናቸው። ከእነርሱ በአንዱ ሰውጥ ሲሆን ብዙውን ጊዜ በሌላቸው

ይህ ክፍል ለቤተክርስቲያን እንደሲስተም የመነሻ ማብራሪያ ብቻነው።

የብዜት መረብ አገልግሎት፤ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ጠንካራ ቤተክርስቲያኖች

የማብራሪያ ዋርካ ሾፕ በሚል የበለጠ በዝርዝር ያቀርባል።

ግብ፦

ተሳታፊዎች የሚከተሉትን እንዲረዱ..

ስለሲስተሞች ፅንሰ ሃሳብ እና አዲስ ቤተክርስቲን ከመጀመር ጋር

ነዴት እንደሚዛመድ ትረዳለች።

የጤነኛ ቤተክርስቲያን አምስት ጠቃሚ ባህርያቶች እና አምስት

ልፍ ተግባሮች ትማራለህ።

ሰዎችን ከመነሻ ገጠመኞቻቸው ወደ መንፈመስና ወደ አገልግሎት

የሚወስድ ሂደት ታቀዳለህ

ለውጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪው ለውጪው ደግሞ÷ እሱ ወይም እሷ በሚኖሩበት በከባው ሁኔታ ሊጎዱ ይችላሉ፡፡ በሽታውን ለመከላል÷ ለይቶ ለማወቅ÷ ሕመሙን ለማከም ብሎም የታካሚውን ደህነት ወደነበረበት ለመመለስ፤ ጥሩ ሐኪም በሰውየው የተለያዩ ንዑህ ሲስተሞች ውስጥ እና በውጭ ደግሞ በከባቢው ሁኔታ ምን እንደተፈጠረ የማወቅ ጠቃሚነት ይረዳል፡፡ ስለቤተክርስቲንም በተመሳሳይ መንገድ ልናስብ እንችላለን፡፡ ቤተክርስቲን አንድ አካል

ስትሆን ከብዙ ንዑስ ሲስተሞች የተሰራች ነች፡፡ በአንድ በተወሰነ አካባቢም ትገኛለች፡፡ ስለተለያዩ የቤተክርስቲያን የሕይወት ክፍሎች በማወቅ እንዴት እነርሱ እርስተ በእርሳቸው ያላቸውን መስተጋብር እና ቤተክርስቲያኗ ያለችበትን ዐውድ በማወቅ መሪዎች ጥበብ የተሞላበት ውሳኔዎች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እናም ቤተክርስቲያኗን እድታድግ ይረዳታል፡፡

## የስልት ቁልፍ መርሆዎች ከቤተክርስቲያን ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ

- ጤናማ መሪዎች፤ ቤተክርሰውቲን ባለሁለት ባህርይ፡- ሕያው አካልና የተዋቀረች ድርገጅት እንደሆነች ይረዳሉ፡፡ መሪዎች በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ እየሰሩ ነገር ግን በአእምሯቸው አጠቃላይ ቤተክርስቲንን መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ጥበበኛ መሪ አይኖቹን ጫካውን ከመመልከት ሳያነሳ ዛፎቹን ያያል፡፡
- የመሪዎች ሃላፊነት /ሚና የአገልሎትን አካል (ሁለ,ሉን አባሎች) እግዚአብሔር የሰጠውን ተግባሮች በማከናወን በራሱ አውድ ለእግዚአብሔር ክብርና የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስቀጠል ማንቀሳቀስ ነው፡፡ መሪዎች የግብአት አጠቃቀም ፤ የቤተክርስቲን የተለያዩ
- የንዑ ሲስተሞች አሰራርን (የትምህርት አገልግሎትን÷የሚዚቃ አገልግሎትን÷ የሴቶችእና የወንዶች (የወጣቶች አገልግሎቶችን ወዘተ) ይቆጣጠራሉ፡፡

እነዚህ አስሩ መሰረታዊ አስፈላጊ ባህርያት ሲሆኑ ለቤተክርስቲያን ጤና በጣም ወሳኝ ናቸው። ሌሎችም በቤተክርስቲያን እድገት ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ነገሮች አሉ፡- እንደመዋቅር÷ መርሃ ግብሮችና ግንኙነቶች ራሷ ቤተክርስቲያን የምትገኝበት ማህበረሰብና መንፈሳዊ ይዘት ናቸው።




## አምስት አስፈላጊ መስጠቶች

ራዕይ፡- ቤተክርስቲያን፤ እግዚብሔር መሆን እንዳለበትና እንደክርስቶስ አካልነቷ እንድትሆን የሚፈልገውን በግልፅ እንድታይ ያደርጋታል። በተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ውስጥ በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ በኢየሱስ ክርስቶስ ሙላትን ለማምጣት ጉባኤው ከእግዚአብሔር የመዋጀት አላማዎች ጋር ራሱን ይወግናል።

የአመራር ቡድን፡- መሪዎች በቤተክርስቲያ ወዳሉበት የአገለግሎት ሹመት የተጠሩት በእግዚአብሔር ነው። የቤተክርስቲንን ራዕይ ተረድተው ለጉባኤ ራዕዩን በግልፅ በማስረዳትና የክርስቶስን አካል ራዕዩን እውን እንድታደርግ ማዘጋጀት ስራቸው ነው።

የቤተክርስቲያን አባልነት፡- የቤተክርስቲያ አባሎች የተሰጣቸውን ስጦታዎች ሀላፊነት በመጠቀም ለጉባኤውና ለህብረተሰቡ ሁለቱንም በመንፈስ ቅዱስ በመመራት አብረው ያገለግላሉ።

ግብዓቶች፡- የቤተክርስቲያ አመራር በግልና በቤተክርስቲያናት የመልካም አገልጋይ ምሳሌ ናቸው። አባሎች የራሳቸውን ሃብትና ንብረት በመልካም እንዲያስተዳድሩ ይፈለግባቸዋል። ቤተክርስቲያን የራሷን ግዜዋን ችሎታዋንና ሀብቷን፤ የእግዚአብሔርን መንግስት ስራ ለማከናወን በቤተክርስቲንና በማህበረሰቡ ውስጥ ትጠቀማለች።

ቃልና ዓውድ፡- ቤተክርስቲያን ያለችበትን ዓውድ (እንደምሳሌ ባህልን÷ ሃይማኖትን÷ የኢኮኖሚ÷ የጂኦግራፊና የማህበራዊ ሁኔታዎችን) ተረዳለች፡፡ እናም የእግዚአብሐየርን ቃል ለአድማጮች በሚረዱበት መንገድ እንዴት እንደምታደርስ ታውቃለች፡፡

አምስት አስፈላጊ ተግባሮች

ወንጌል ስርጭት፡- ቤተክርስቲያ የመንግስቱን መልም ዜና በቃልና በተግባር ታበስራለች፡፡ ቤተክርስቲያ ሰዎችን የኢየሱስ ደቀመዛሙርቶች እንዲሆኑ ተጋብዛለች እናም ለስአዲስ ፍጥረትነት ታመሳክታለች፡፡

ደቀመዛሙርት ማድረግ፡- ቤተክርስቲን ለሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን በግልፅ መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው እንድናደለነሱ ፍቃድን በመግለፅ እና በመንፈስ ቅዱስ እየተመራን በሁሉም የሕይወት አቅጣጫ እንድንከተለው በማድረግ ተረዳናለች፡፡

አገልግሎት፡- ቤተክርስቲያ የሰዎንና የማህበረሰቡን ፍላጎቶች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በተቀደሰ አኳኋን ታሟላለች፡፡ ሰዎች የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ ትጋብዛለች፡፡

ህብረት፡- አባሎች እርስበእርሳቸው የእግዚብሔርን ፍቅርና ርህራሄ ያሳያሉ፡፡ ደስታዎቻቸውንና መከራቸውን ይከፋፈላ፡፡ የፀሎት ሕይወት ማህበረሰቡን በአንድነት ያጣምራቸዋል፡፡

አምልኮ፡- ቤተክርስቲን እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የእግዚአብሔርን መልካምነትትልቅነት ለማወደስ÷ ንስሃ ለመግባት÷ እና በምስጋና ምላሽ ለመስጠት ቃሉን በመስማትና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሕይወት አገልሎት ራሳቸውን በመስጠት ቃል ለመግባት ትሰበሰባለች፡፡

ቤተክርስቲያንን የሚተክሉ አብረው ከመሪዎች ጋር ይሰራሉ፡፡ አስረን ገፅታዎች የቤተክርስቲንን ሕይወት ቆጣጠራሉ፡፡

## ለ. ቤተክርስቲያን እንደ ሲስተም/ስርዓት

ሲነስ ሞሪስ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድረ ቤተክርስያኖች በሚለው መፅሐፍ፡- እርሱ ባሳቀና በሚያድጉ ቤተክርስቲኖች የተገነዘበውን ዘጠኝ

ይህ ክፍል በቁልፍ ተግባሮች ላይ ስራቸውን ለማደራጀት ቤተክርስቲያኖች የሚጠቀሙበትን የንዑስ ስርአት ሌላ መዋቅር ይሰጣል።

አስፈላጊ ባህርያቶች አካፍሎናል እነዚህ ባህርያት እኛ እንደቤተክርስቲያን ንዑስ ሲስተሞች ልናያቸው እንችላለን።

1. **የመማለድ ስርአት፡-** ዋነኛና ወሳኙ ሲተም የምልጃ ፀሎት ነው። ጉባኤው በጋራ ከህዝቡ ጋር የፀሎት ጊዜዎች ይኖረታል። አባሎችና መሪዎች የበሰፀገ የግል የፀሎት ሕይወት አላቸው። ለቤተክርስቲያን አገልግሎት አደግሞ እንዲፀልዩ የተመደቡ አማላጆች።
2. **የወንጌል ስርጭት ስርአት፡-** ይህ ቅድመ ወንጌል ስርጭት እንቅስቃሴዎችን÷ በግለሰብ የሚደረጉ የወንጌል ምስክሮችን÷ የወንጌል ስርጭት በዓል እና አለም አቀፍ ራዕይ ያካትታል።
3. **የማዋሃድ ስርአት፡-** የማዋሃድ አላማው አዲስ አባሎችን ችሎታቸውን ለማዳበር አባሎችን ተስማሚ አገልግሎት ውስጥ በመንፈሳዊ ስጦታዎቻቸው ላይ በመመርኮዝ እንዲሳተፉ በማድረግ ለመርዳት ነው።
4. **መንፈሳዊ ምግብ የመመግ ስርአት፡-** ይህ ዋናውን የአምልኮ አገልሎት ወይም የቤተክርስቲያንን ስብሰባ ይመለከታል። ዋናዎቹ ተሳታፊዎች አባሎች ናቸው። ፓስተር፤ አስተማሪው፤ የአምልኮ መሪዎች መርሃ ግብሩን የሚመሩትን የሙዚቃ ሶችን፣ አስተማሪዎችንና ቴክኒካል ሰዎችን የድጋፍ አገልግሎት የሚሰጡትን እግዚአብሔርን ለመስማትና ምላሽ ለመስጠት ጉባኤውን ይረዳሉ።
5. **አመራሩን የማልጠን ስርአት፤ የመሪዎች ቡድን፡-** ፓስተሮች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆኖችና ሌሎች መሪዎች ሊያካትት ይችላል። የአመራር ሲስተም ኃላፊነት ለሌላው ለቀረው አካ ራዕዩን ማካፈል እና አባሎችን ለአገልግሎት ማንቀሳቀሰው ናቸው።
6. **የአስተዳደር ስርአት፡-** ብቁ የሆነ የአስተዳደር ሲስተም ራዕዩን ይለያቸዋል። ዓላን ያስቀምጣል÷ ግቦችን ለመምታት እቅድ ያዘጋጃል። መሪዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰበስባሉ። እና የመነሻ ነጥቦችን፤ ቤተክርስቲያ ወዴት መሔድ እንደሚያስፈልጋት እናም እዛ እንዴት እንደምትደርስ ይወስናሉ። ምርጥ የጊዜንና የግብአትን አጠቃቀም ያዘጋጃሉ።እናም ወደአንዳንድ ግብ የተደረገውን ምዘና ይመዝናሉ።

7. **የኮሚኒኬሽን/ የግንኙነት ስርአት፡-** ጉባኤው እያደገ ሲመጣ መሪዎች መደናገርና ውጤት አሳባነትን ለመከላከል ግንኙነቶችን የበለጠ በስርዐት እዲሆኑ ያስፈልጋል። የኮሙኒኬሽን ቡድኑ አንዱን መረጃ ወደአባሉች እንደሚደርሱ ይቆጣጠራል። (ለምሳሌ በመግለጫ፣ በመፅሔት፣ በፅሑፍ መልእክት በዌብ ገፅ፣ በማስታወቂያ፣ በበሬ ወረቀት በኢሜል ወዘተ)
8. **የፋይናንስ /የገንዘብ አስተዳደር ስርአት፡-** መሪዎች የቤተክርስቲያን ፍይናንስ በተስማሙነት የሒሳብ አስተዳደር ደንቦች መሰረት የመጠቀም ሃላፊነት አለባቸው። ያልታጠረ ፋይናንስ፤ በግልፅነት እንዴት ስለቤተክርስቲን ገንዘብ አጠቃቀም መረጃ መስዋወጥ ለቤተክርስቲን ጤንነት ወሳኝ ነው።

## የትግበራ ዕቅድ

1. የአገልሎትህን ዋና መርሆች፡- ግብሮች ዘርደዝራቸው

| | |
|---|---|
| ______________________________ | ______________________________ |
| ______________________________ | ______________________________ |
| ______________________________ | ______________________________ |
| ______________________________ | ______________________________ |
| ______________________________ | ______________________________ |
| ______________________________ | ______________________________ |

2. ከዚህ በታች ባለው ተስማሚ ካታጎሪ/ክፍል እያንዳንዱ መርሃ ግብር ዋና ዓላማ አድርጎ በያዘው መሰረት ዘርዝሯቸው። ጥቂት መርሃ ግብሮች ከአንድ የበለጠ ካታጎሪ/ክፍል ውስጥ ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእያንዳንዱ ካታጎሪ/ክፍል መግለጫቸውን ከዚህ በታች ተመልከት።

| ሰዎችን ማቀፍ | ሰዎችን መገንባት | ሰዎችን ማስታጠቅ | ሰዎችን ማንቀሳቀስ |
|---|---|---|---|
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |
| ________________ | ________________ | ________________ | ________________ |

1. **ሰዎችን ማቀፍ፡-** ሰዎችን ወደአንተ ጉባኤ ያገኙበት መንገዶች የእንኳን ደህና መጣችሁ ስሜት እንዲሰማቸው ማድረግ፤እና ወደኢየሱስ ክርስቶስ ግንኙነት/ህብረት ጋብዛቸው፡፡

ምሳሌዎች፡- ወደልዩ የአምልኮ አገልግሎቶች ኮንሰርቶች ወይም የመዝሙር ዝግጅቶች የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ክርስቲያ ካልሆኑ ሰዎች ጋር የጓደኝነት ዝግጅቶች ቤተሰቤት ወንጌል ስርጭት ወዘተ...

2. **ሰዎችን መገንባት፡-** ሰዎችን ደቀመዛሙርት የምታደርግበትና በእምነታቸው እንዲያዩት የምትረዳቸው መንገዶች ምሳሌዎች፡- የፀሎት አጋሮች፣ በትምህርት ክፍል አዲስ አባሎች መጨመር፤ የሴቶች አገልግሎት፤ የወጣቶች አገልግሎት፤ ግንኙነቶችን ለማደስ የሚሰሩ ሜንቶሮች/አማካሪዎች
3. **ሰዎችን ማስታጠቅ፡-** ሰዎችን ስጦታዎቻቸውን እንዲለዩ እና እንዲያሳድጉ የምትረዳበትና ሰዎችን ለተለያዩ አገልግሎቶች የምታሰለጥንበት መንገዶች ምሳሌዎች፡- የወንጌል ስርጭት፤ ምርክ ሾፕ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ላይ ለቤተሰብ በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ሴሚናሮች መስጠት፤ አምልኮ በመምራት እና በስብሰባ ላይ ስልጠና መስጠት፤ ለትንሽ ቡድን መሮዋች ስልጠና መስጠት፤ የጊታር ትምህርት መስጠት፤ ለሽ ማግሊዎችና ለዲያቆናት ስልጠና ወዘተ...
4. **ሰዎችን ለአገልሎት ማንቀሳቀስ፤** ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎቻቸውን ባንተ ጉባኤ መካከል እና በውጭ እንዲጠቀሙባቸው የምታደርግበት መንገዶች፤ **ለምሳሌ፡-** የምግብ ዝግጅት፣ ቤተሰቦችን መጎብኘት፣ ማስተማር፤ መዝሙሮችን በአምልኮ መምራት፣ እነርሱ ኀበዝ በሆኑበት የተወሰኑ እንቅስቃሴዎችን፣ ክፍልን መምራት፣ ለጎረቤት ልጆች የእግርኳስ መዝናኛ ማዘጋጀት፣ የአምልኮ ቦታን ማፅዳት፣ ለሕብረተሰቡ የአምልኮ እንቅስቃሴ ማድረግ ወዘተ... ማንኛውንም ነገር የሰው ልጆች ሊሰሩት የሚችሉት በአብዛኛው በቤተክርስቲያን አገልሎት ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡

ይህን ሒደት ከመሪዎች ጋር በቤተክርስቲን እንድትደግመው እናም በእያንዳንዱ ያንተ መርሃ ግብሮች የሚጠይቁትን የመስጠት ደረጃ እድትወስን እንመክራለን፡፡

# ክፍለትምህርት 9

# መሰናክልን መቋቋም

“በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንደሆነላችሁ ይህን ተናግሬያችኋለሁ፡፡ በአለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ አለምን አሸፌዋለሁ፡፡”

አዲስ ቤተክርስቲኖች ቢሮቻቸውን የሚዘጉ ለመጀመሪያ ሁለት ከመቶኛ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ለቅድመ ብቃት መዘጋት ብዙ ምክንያቶች አሉ፡- የሰነ ምግባር ውድቀት ደካማ እቅዶችና ሌሎች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የአዲስ ቤተክርስቲያንን ትግሎችና እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል በተለያዩ ምክንያቶች እንለየዋለን፡፡

አንዳንዱ ቤተክርስቲያን የሚተክል አገልጋይ አጀንዳ ከዋናው ቡድን አባሎች ካላቸው ጋር የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለያ ሁኔታዎች የዋናው ቡድን አባሎች የመሪውን አጀንዳ ሳያውቁ ይችላሉ፡፡ እነርሱ ግን ተመሳሳይ ሀሳቦች ያላቸው ይመስላቸዋል፡፡ የተለያዩ አጀንዳዎች ግጭቶችን፣ ችግሮችን፣ ተስፋ መቁረጥና መከፋፈልን ይፈጥራሉ፡፡ ሰዎች ራዕያቸውን የሚያካፍሉ፤ በራሳቸው አመለካከት እና አስተሳሰቦች

ተሳታፊዎች የወጣት/የአዛውንት ሴት ፎቶ እንዲያዩ አድርግ እና ምን እንዳዩ ጠይቃቸው፡፡ አንዳንዶች አዛውንት ሴት አየን ይላሉ፣ አንዳንዶች ወጣት ሴት አየን ይላሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ሁለቱንም ይላሉ፡፡

ለለቤተክርስቲያን በሚኖሩት ውይይቶች ተመሳሳይ ነገር እንደሚከሰት አብራ፡፡ እያንዳንዱ ሰው ሁኔታዎችን ከራሱ ወይም ከራሷ አመለካከት ነው፡፡ ሌሎች ም ማድረግ እንዳለባቸው ደግሞ እሳቤ አላቸው፡፡ ስለዚህ ውሳኔዎች በሚሰጡበትና ለአለመግባቶች መፍትሄ በምንፈልግበት ወቅት ወደ አገልግሎት፤ ራዕይ ተልዕኮ ማየት ያስፈልጋል፡፡

አሉታዊነት ለቡድኑ ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡ እናም ለቤተክርስቲያን ተልእኮ የማሰናከያ አለት ሊሆን ይችላሉ፡፡ እናም ለቤተክርስቲያን ተልዕኮ የማሰናከያ አለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡



ግቦች ፡-

ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ይረዳሉ…

- ቤተክርስቲያንን ለመጀመርና ለማደግ መሰናክል የሚሆኑ ምክንያችን መለየት
- አግላዊ አቀራረባቸው ወደ ግጭት የሚያመሩትን ማስገንዘብ /ሪፍሌክት ማድረግ፡፡
- ለግጭቶች መፍትሔ የሚሰጥበገትን ሂደት መማር፡፡

አብረን የእግዚአብሔርን ፍቃድ በጋራ የምንፈልግ ከሆነ ችግሮችንና ግጭቶችን መቋቋም ይቻላል፡፡

*“ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ ሀሳብም የተባራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ፡፡” 1ኛ ቆሮ 1፡10*

ጳውሎስ ስለመከፋፈሎች ሲናገር እርሱ "ጥንድ ራዕዮች" ማለቱ ነው፡፡ የራስህ ራዕይና ግቦች መኖረ መጥፎ አይደለም፡፡ ነገር ግን በራስህ የግል ራዕይ ላይ ብቻ ካተኮርክ፤ የቤተክርስቲያንን አካል ራዕይ ካላከበርክ እና ከግንዛቤ ውስጥ ካላካተትክ የዚያን ጊዜ መጥፎ ይሆናል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስን መሰረት ያደረገ የጋራ ራዕይ እና በግልፅ የተብራራ ተልዕኮ በተደጋጋሚ የምጠቀምባቸው እና ለውሳኔዎች መሰረት ሆነው የሚያገለግሉ ከሆነ አለማግባባቶችን በመከላለክ ሊረዱህ ይችላሉ፡፡

ይህን ክፍል ከማንበባቸው በፊት ተሳታፊዎችን ለአዲስ ቤተክርስቲያን እድገት መሰናክል የሆኑትን ነገሮች እንዲዘረዝሩ ጠይቃቸው፡፡ እነዚህን በትልቅ ወረቀት እንድትፅፍላቸው እናም እዚህ ተሰጥተው ከወጡት ምክንያቶች ጋር አወዳድራቸው፡፡

## ሀ. ለአዲ ቤተክርስቲያ እድገት መሰናክል የሚሆኑ ምንያቶች

1. መሪው ቤተክርስቲን ለመትከል በትክክል የተሟላ ስጦታዎች የሉትም፡፡
2. የዋናው ቡድን ብቃት ማነስ
3. የእቅድ ስህተት
4. በመሪዎች መካከል የቁጥጥር የድጋፍ እና የተጠያቂነት መነስ

5. በአመራረ መካከል የሚገኝ ኃጢያት
6. የፋይናንስ እጥረት
7. ሊሳ ያደረግነውን ቡድን አለመረዳት
8. ትክለኛ ያልሆነ ነገር መጠበቅ
9. ለወንጌል ስርጭት እና ለደቀመዛሙርት ማፍራት ትኩረት አለመስጠት
10. አገልግሎቱን ሳማሳካት አጠቃሳይ የስትራክቸው አለመሟሳት

ቡድኑን በጥንድ ክፈሳቸው እያንዳንዱን ቡድን ከመሰናክሉቹ አንዱን በሲክሽን ሀ ከተመዘገቡት (በእናንተ ቤተክርስቲያን አውድ ያሉትን ልዩ ችግሮች እንዲወስዱ) መድባቸው ጥንዶቹ በሶስት መንገድ እንዲወስኑ ንገራቸው፡፡ ችግሩ ሊወገድ አይችልም፣ ይእሳል ወይም መፍትሄ ሊያገኝ ይእሳል፡፡ በሚል ከዛ በኋሳ እያንዳንዱ ጥንድ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ጠይቃቸው፡፡

## ለ. ግጭቶች በቤተክርስቲያን

- ግጭቶች አይቀሬ እና የሕይወት ገጠመኝ አካል ነው፡፡
- ለግጭት እንዴት ምሳሽ መስጠት እንዳለብን መምረጥ እንችሳለን፡፡
- ራዕይ እና ተልእኮ በትኩረታችን ሳይ እንድንቅይ ሊረዱን ይችሳሉ፡፡ እነርሱ በቤተክርስቲያን ራዕይ እና ተልእኮ የማይስማሙ ከሆነ እኛ ቤተክርስቲያኗን ለቀው እንዲሄዱ ልንፈቅድሳቸው ይገባል፡፡

ምንም እንኳን ሁሉም በራዕዩ ቢስማሙም ግጭት አይቀሬ ነው ለግጭቱ መፍትሔ የሚሰጥበት መንገድዋናው ቡድን ራዕዩን ለማሳካት ወደፊት በመገስገስ ይቀጥሳል ወይስ? የሚለውን ጥያቄ ይወስነዋል፡፡

**አስታውስ፤ መሪው የተለየ ዕይታ ቢኖረው ሃጥያት አይደለም፡፡ ኃጥያት ግጭትን በመፅሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ አለመፍታት ነው፡፡**

## ሠ. የግጭት ምክንያቶች

1. ግልፅ ያልሆኑ ግቦች፡- ሰዎች ራዕይ ምን እንደሆነ እና እንዴት ወደ እሱ እንደሚሰራ አያውቁም፡፡ ራዕይ እሴቶችና ተልእኮዎች በግልፅ ካተቀመጡ አለመግባት ከመሪዎች መካከል ይፈጠራል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ግባዊ አጀንዳ አለው፡፡ ነገር ግን ዋናው የአመራር ቡድኑ የጋራ አጀንዳ ሊኖረው ይገባል፡፡

2. <u>የግንኙነት</u> ችግሮች፡- ዋናው ቡድን ራስዩ፣ ተስስኮ፣ ውሳኔዎች በሚገባ ስቤተክርስውቲያ ማስገንዘብ ካልቻለ አባሎች አንዳንድ ውሳኔዎች ለምን እንደተደረጉ ሊረዱ አይችሉም፡፡

3. <u>በአደራረግ</u> የሚፈጠሩ ልዩነቶች፡- የሰዎች የተለያየ አቀራረብ ስተግባሮች እና ለችግሮች የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዴም የማይጣጣም መንገድ ነው፡፡

4. <u>በማንነት</u> የሚፈጠሩ ልዩነቶች፡- ሰዎች አንዱ ከሌላው ጋር የሚቀራኙበት እና ለሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡበት መንገዶች የተለያዩ ናቸው፡፡

5. <u>ኃጢያት፡-</u> ሰዎች የሚናገሩት እና የሚያደርጉት ተግባራት ሌሎችን ይጎዳል፡፡ አንዳንዱ ሳያድቡት እንኳ ያደርጉታል፡፡

## ሰ. የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ ቤተሰቦች የሚጋፈጧቸው አደጋዎች

- የወሰን አለመኖር ከፈቀድክለት አገልግሎቱ እና ፍላጎቱ ሁሉን ያንተን ጊዜና ጉልበት ይጨርሰዋል፡፡ ያንተን ወይም የሌሎችን ይሆኑልናል ብላችሁ የምትጠብቋቸው ነገሮች ለማሟላት ጥረት ማድረግ
- ከባለቤትህ÷ ከቤተሰብህ ወይም ከጓደኞችህ ጋር ካለህ የጠበቀ ግንኙነት የተነሳ፤ የአገልግሎቱን ስራ በነሱ መተካት፡፡
- ከቤተሰብና ከጓሰኞች ድጋፍ ርቀህ በአዲስ እና በማታውቀው ሃገር መኖር፡፡

ጥያቄዎቹን ከመለሱ በኋላ ስለራሳቸው ምን እንደተማሩ ለይተው እንዲያወጡ ጠይቃቸው፡፡

## ሰ. መፅሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለአንድነት እና ግጭትን ስለመፍታት ምን ያስተምሩናል?

- “ወንድሞች በክብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው እነሆም ያማረ ነው፡፡” መዝ 133፡1
- *"ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።"*

ዮሐ 17፡ 20-23

- "ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ።" 1ኛ ቆሮ 1፡10
- "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።" ኤፌ 4፡3
- "ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ። ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።" ኤፌ 4፡25-27
- "እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።" ኤፌ 4፡32

## ፈ. ለግጭቶች የሚሰጡ ሶስት ምላሾች

ግጭቶች ሰዎች በጣም ምቹ እንዳይሆኑ ሲያደርግ ይችላሉ፡፡ በመደነቅ ይወስደን እና በኋላ የምናዝንበት ነገር እንድንናገር ወይም እንድናደርግ ያደርገናል፡፡ አንድ ሰው ሲያበሳጨን ሳናስብ ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን፡፡ በድንገት ይህም ከኮረብታ ወደታች በሚያዳልጥ ቁልቁለት እንደምንንሸራተት ነው፡፡ እናም ነገሮች ከመጥፎ ወደባሰ ይሄዳሉ፡፡ በሚቀጥለው ገፅ ስዕሉ እንደሚያሳየው ወደተሳሳተ አቅጣጫዎች ልንገዝ እንችላለን አንድም ከግጭቱ ልንሸሽ እንችላለን ወይም የበለጠ ግጭቱን እናባብሳለን፡፡ ነገር ግን ትክክለኛ ግጭትን መቆጣጠሪያ ሰላም ማድረጊያ መፅሐፍ ቅዱሳዊ መንገቸድ አለ፡፡

### ለግጭቶች የሚሆኑ ሶስት መልሶች

1. ከችግሩ ማምለጥ

- መካድ
- መሸሽ
- ራስን ማጥፋት

2. ማጥቃት

- በስጋ መገለጥ ወይም መሳደብ
- ጉዳዩን ወደህግ ማቅረብ
- መግደል

3. ሰላም መፍጠር

ሀ. ግላዊ ሰላም መፍጠር

- ነገሩ እንዲቀጥል መፍቀድ
- ውይይት
- መደራደር

ለ. ሰላም ለመፍጠር የሚረዱ ዘዴዎች

- ማስላሰል
- መዳኘት
- የቤተክርስቲያን ስርአት ህጎች



## ሸ. ለግጭት የሚሰጡ ሶስት ምላሾች እና ውጤታቸው

| ባህርይ | ሽሽት | ሰላም መፍጠር | ጥቃት |
|---|---|---|---|
| ውጤት | አንተ አሸንፈሃል እኔ ተሸንፌያለሁ | እኔም አሸንፌያለሁ አንተም አሸንፈሃል | እኔ አሸንፌያለሁ አንተ ተሸንፈሃል |

## ቀ. ግጭቶችን የማስተዳደር ሂደት

1. ችግሮችን መለየት እና ማብራራት ሰዎች ምን እንደሚያስቡ ችግሩ ምን እንደሆነና ስለሁኔታው የሚሰማቸውን እንዲገልፁ ጊዜ ስጣቸው፡፡
2. አማራጭ መፍትሔዎችን መፍጠር፡፡ ስለአማራጭ መፍትሄዎች አብሮ ማሰብ የእያንዳንዱን ጥቅምና ጉዳት ተነጋገሩበት፡፡
3. ውሳኔዎችን ማድረግ፡- የላቀውን አማራጭ ምረጥ
4. ለውጥን በስራ ላይ ማዋል፡- ሰዎችን ስለሚያደርጉት ነገር ተጠያቂ ማድረግ
5. መመዘን፡- የተወሰዱት እርምጃዎቹ የታሰበውን ውጤት አምጥተው እንደሆነ መወሰን፡፡ በተግባር እርምጃዎች በዚህ ትምህርት መጨረሻ ምሳሌያዊ ግጭት በመለየት እና ይህን ሂደት በመጠቀም ግጭቶችን አስተዳድራቸው፡፡

## የተግባሩ ዕቅድ

1. ባጠቃላይ ግጭቶች ሲነሱ ለመሸሽ የመሞከር አዝማሚያ አለህ ወይ? ቁጡ ትሆናለህ ወይንስ በተለየ መንገድ ምላሽ ትሰጣለህ?

2. ከሌላ ሰው ጋር የነበረህን የቅርብ ጊዜ ግጭት አስብ (ወይም የቅርብ አጋጣሚ አንዱ እንደእብድ ያደረገህ) ግጭቱ ስለምን ነበር? እንዴት ነው  ምላሽ የሰጠኸው? (ሰላም ለማድረግ መሞከር?) ወደፊት ምን የተለየ ነገር ነው ልታደርግ ያሰብከው?

3. የቡድን አባሎች ይኑረህ እና በቤተክርስቲያን በአይነታቸው የሚነሱ የግጭት ምሳሌዎችን አካፍላቸው:: አንዱን ውሰድና ለተሳታፊዎች ምን እንደሚያደርጉ መድባቸው:: በሴክሽን ሰ (ግንኙነቶችን የማስተዳደር ሂደት) ያሉትን ደረጃዎች በመጠቀም በግጭቶች ውስጥ ስሩ::

# ክፍለትምህርት 10

# ራስህን እና ቤተሰብህን ተንከባከብ

*"አባቶች ሆይ፥ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው።" ቆላ 3:21*

ቤተክርስቲያንን የሚተክሉ ሰዎች ለቤተሰቦቻቸው ቀድሚያ ሊሰጡአቸው ይገባል፡፡ ዩገባህ ከሆነ ከፍተኛውን ዋጋ ለልጆችህና ለባለቤትህ እንክብካቤ መስጠት ይኖርብሃል፡፡ ያስመታደል ሆኖ ብዙ ቤተክርስቲያን የሚተክሉ ሰዎች 24 ሰዓት በቀን ራሳቸውን ለአገልግሎታቸው እና ለሌሎች ሰዎች ፍላጎቶች ሲያውሉ ለቤተሰቦቻቸው ግን እንግዶች ሲሆኑ ይታያሉ፡፡ ያላገባህ ብትሆን እንኳ አሁንም ቢሆን ራስህን ለመንከባከብ ወሰኖች ልታበጅለት ይገባል፡፡ ጤናማ ግንኙነቶች ይኑርህ እናም ራስህን ከግምት ውጭ አታድርግ፡፡

## ሀ. የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች እና ቤተሰቦቻቸው የሚያገኙት ጥቅም

ቤተክርስቲንን መትከል የሚከተሉትን እቅድ ያዘጋጃል፡፡

- የሌሎችን ዋናና መሰረታዊ ስነ-አእምሮአዊ ፍላጎቶችን ያሚላል፦ ማፍቀር እና መፈቀርን የጠቃሚነት ስሜት ለራስ እና ለሌሎች፡፡
- እንደመፈ ማደግና መመንደግ

ይህንን ክፍል ከማቅረብህ በፊት እንዴት ቤተክርስቲያን የሚተክል ሰው እና የእሱ/ሷ ቤተሰቦች ቤተክርስቲያን በመጀመራቸው ሊባረኩ ስለሚችሉበት ሃሳቦች አድንዲያካፍሉ ጠይቃቸው፡፡ ሶስት ወይም አራት ሰዎች በቡድን ሆነው ይህንን እንዲያካፍሉ አድርጋቸው፡፡ በልብህ ያዘው ይህ ብቻ አይደለም ተሳታፊዎች የተጋቡ ሊሆኑ ይችላሉ አንዳንዶቹ እግዚአብሔር የጠራቸው በብቸኝነት እንዲያገለግሉት ነው፡፡ (1ቆሮ 7:1፣ 7:8፣17)እናትና አባት እህት ወንድም እና ጓደኞች በመመገብና በመንከባከብ ሰብቸ፣ ቤተክርስቲን ለሚተክል ሰው ወሳኝ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡

ግቦች

ተሳታፊዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ

- ቤተክርስቲያን ለሚተክል ሰው ቤተሰብ የሚጠቀሙት ጥቅሞች እና አደጋዎች ተወያይባቸው፡፡
- እንዴት ራሳቸውን እና የእነርሱን ቤተሰቦች እንደሚንከባከቡ አቅድ፡፡

አንድ መጋቢ የራሱን ወይም የራሷን ቤተሰብ ችል ሲሉ አይተው እንደሆን በመጀመሪያ ደረጃ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ተሳታፊዎቹን ጠይቅ፡፡

- ሰዎችን በእጅግ ወሳኝ የሕይወት ሁኔታዎቻቸው ማገልገል፡- በጋብቻዎቻቸው፣ በልደቶቻቸው፣ በቀብራቸው ወ.ዘ.ተ
- ተመልከት እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ይሰራል፡፡ እና በመንፈስ የጠፉ ሰዎች እዩ ሕይወታቸውን ወደክርስቶስ ዘወር ያደርጋሉ፡፡
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችህን አሳድግ እናም ቤተሰብህ የፀጋ ስጦታዎቻቸውን እንዲያሳድጉ እርዳቸው፡፡
- የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ መሆን ማለት ላንተ ለልጆችህ እና ለዘመዶችህ ሞዴል ምሳሌ ሁናቸው ማለት ነው፡፡
- ሌሎችን በወንጌል ለመድረስ የምችት ቀጠናህን ተተህ ውጣ፡፡

## ለ. ቤተክርስቲያን ለሚተክሉ ሰዎች/ቤተሰቦች ሊገጥሙ የሚችሉ አደጋዎች

- የውስንነት አለመኖር፡፡ ከፊቀድክለት አገልግሎቱ እና ፍላጎቱ ሁሉንም ያንተን ወይም የሌሎችን ይሆኑልናል ብላችሁ የምትጠይቋቸው ነገሮች ለማሟላት ጥረት ማድረግ፡፡
- ከባለቤትህ፣ ከቤተሰብህ ወይም ከጓደኞችህ ጋር ካለህ የጠበቀ ግንኙነት የተነሳ የአገልግሎቱን ስራ በአነሱ መተካት፡፡
- ከቤተሰብህ እና ከጓደኞች ድጋፍ ርቀህ በአዲስ እና በማታውቀው አካባቢ መኖር፡፡
- አብሮ ከቤተሰብ ጋር የማደግን ዕድሎች አለመጠቀም፡፡
- ብዙ ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር በስሜት በመሰማራት አንዱ ከሌላው ጋር አብሮ መኖርን ማጎልበት፡፡
- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል (አንተን ጨምሮ) ሃሳባቸውን እና ስሜታቸውን የሚገልፁበት አስተማማኝ ቦታ ሊስማመዱበት የሚችሉት መቦረያ ቤታቸው ውስጥ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ታዲያ ቤት እንዲህ ላለው ነጻነት የተመቸ ካልሆነ የበተሰቡ አባላት ደስተኛ የሚያደርጋቸው ምን አይነት ስፍራ ይገኛል፡፡

## ሠ. ለራስህ ጥንቃቄ እና እንክብካቤ ማድረግ

ክፍል ሠን ካነበብክ በኋላ በትምህርት 10 ላይ ያሉትን ጥያቄዎች የድርጊት ዝርዝር ቁጥር 1ድን ተሳታፊዎቹ እንዲመልሱ አድርግ። ጥያቄዎቹን ከመለሱ በኋላ ለስራሳቸው ምን እንደተማረ ለይተው እንዲያወጡ ጠይቃቸው።

ክፍል ሠ እና ሰ ሆን ተብለው አጠር ያሉ ናቸው ስለዚህ ብዙ ጊዜ ለተሳታፊዎች ማዋል ይችላል። በድርጊት ዝርዝር እንቅስቃሴዎች የግል አመለካከት ሊንፀባረቅ ይችላል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቂቱ ትእዛዝ የትኛዋ ነች ተብሎ ሲጠየቅ እንዲህ አለ የመጀመሪያዋ አምላክህን ማፍቀር፤ ሁለተኛዋ ጎረቤትህን እንደራስህ አድርገህ ማፍቀር (ማር 12፡30-31) ራስህን አትውደድ አላለም ይልቁንም ራስህን መውደድ ጤናማ የሰው ልጅ ባህርይ እንደሆነ አድርጎ ነው የገለተው። ሰዎች በኑሯቸው ሲጓዙ የደህንነት መመሪያ የኦክስጅን ጭምብሎቹን አድርግላቸው ነው የሚለው። ምክንያቱም በቂ ኦክስጅን አንተ ካላገኘህ ሌሎቹን በዙሪያህ ያሉትን ማንንም ልትረዳ አትችልም። በተመሳሳይ መርህ ነው ለቤተክርስቲያን የመትከል አገልግሎት የተጠቀምነው። ቤተክርስቲያን የሚተክሉ ሰዎች የአገልሎትን ፍላጎት ለማሟላት እንዲችሉ ለራሳቸው የግዴታ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

## ሰ. ጥንቃቄ ለቤተሰብህ ማድረግ

ክፍል “ሐ” ን ካነበብክ በኋላ በትምርት 10 ስር ያሉትን ጥያቄዎች የድርጊት ዝርዝር ቁጥር 1ን ተሳታፊዎቹ አዲመልሱ አድርግ

የትዳር ጓደኞቻችንን እና ልጆቻችንን እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ብንነግራቸው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ባናሳያቸው፡- አብረናቸው ጊዜ ባንወስድ፣ ሲያወሩን ባንሰማቸው አብረናቸው ባንስቅ፣ አብረናቸው ባናለቅስ፣ ባናገለግላቸው፣ ሕይወትን አብረን ባንካፈላቸው እነርሱ እኛን ሊያምኑን አይችሉም።

ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዳፈቀራት ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲያፈቅሯቸው አዟቸዋል (ኤፌ 5፡25)። የዘዳግም መፅሐፍ ወላጆች ለልጆቻቸው ስለእግዚአብሔር እንዲያስተምሯቸው አዟል። በቤትህ ስትቀመጥ፣ በመንገድህ ስትሄድ፣ ስትተኛ፣ ስትነሳ ዘዳ6፡7 ይህን ሁሉ ለማድረግ በአካል እና በስሜት በሁለቱም መገኘትን ይጠይቃል። በስሜት መገኘት

ማለት ሌሎች የሚያስቡት እና የሚሰማቸው እንደእነርሱ ማሰብና መሰማት ማለት ነው፡፡ እናም እንዴት እንዳሉ ለመጠየቅ ጊዜ መውሰድ የሚሉትንም ከልብ ማዳመጥ ይገባል፡፡

ማስታወሻ፤ ጊዜ ቢፈቅድና የወርክሾፕ መሪው ከተስማማ ተጨማሪ መግለጫ 1ን ክፍል ሐ ን ቤተሰብን እናንብብ፡፡

# የድርጊት ዝርዝሮች

1. ስለራስህ ጥንቃቄ ማድረግ ራስህን በሚከተሉት ርዕሶች መዝን
1= በእውነት አይደለም እና 5= በእርግጥ አዎ

I. ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር

ሀ. በእያንዳንዱ ቀን የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በመፀለይ ጊዜ እወስዳለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

ለ. መንፈሳዊ ምክር የሚሰጠኝ እኔ ለሱተጠያቂነት ያለበት ሰው አለኝ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

2. አካዊ ደህንነት

ሀ. የሰውነት እንቅስቃሴ አደርጋለሁ፣ በሚገባ እመገባለሁ፣ በቂ እረፍት አገኛለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

ለ. በሚያመኝ ጊዜ አርፋለሁ ወይም የህክምና እርዳታ አገኛለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

3. ስሜታዊ ደህንነት

ሀ. በምቆጣ ጊዜ ቁጣውን የምቆጣጠርበትና ሁኔታዎችን የማስተዳድርበት አዎንታዊ መንገዶች አሉኝ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

ለ. ጎበዝ፣ የእግዚአብሔር ቃል የምወዳቸውና ጓደኞቼ፣ እረፍት እና አምልኮ ደስታዬን ይመልሱልኛል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

4. ግኑኝነቶች

ሀ. የጠበቀ ግኑኝነቶች ከቤተሰብና ከጓደኞቼ ጋር አለኝ ጊዜም እወስዳለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

ለ. እኔና ባለቤቴ ወይም እኔና ጓደኛዬ ደስተኞች እና ችግሮቻችንን የምንጋራ ነን፤ አንዳችን በሌላችን መታመን እንደምንችልም እናውቃለን።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

5. የገንዘብ ይዞታ

እኔና ቤተሰቤ ሕይወታችንን ለመምራት እንዲበቃን ገንዘባችንን በሚገባ እናስተዳድራለን።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

6. ዕድገት

ባለፈው አመት አዲስ ነገር ለመማር እድሉን ተጠቅሜያለሁ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

II. ስቤተሰብ እንክብካቤ ማድረግ አንተ ያሳገባህ ከሆንክ እነዚህን ጥያቄዎች ከቤተሰብህ እና ከቅርብ ጓደኞችህ አንፃር መልስ ስጥ

1. ስለራዕይህ፣ ስለአዲሱ ቤተክርስቲያን ዕቅድ፣ ስለጋብቻህ፣ ስለቤተሰብህ እና አብሮ ስለመኖር፣ ከባለቤትህ ወይም ከቤተሰብህ ጋር ከተነጋርክ እና ከፀለይክ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?

2. በመደበኛ አንድ ሳምንት ጊዜ ባጠቃላይ ከቤተሰቡ በግል ደግሞ ከአንዱ አባል ጋር ጊዜ የምትወስደው መቼ ነው?

3. የሚስትህ/የባልሽ ቤተሰቦች ስለቤተክርስቲያን መትከል ያላቸው ፍላጎቶች ምንድን ናቸው?

4. ስለቤተክርስቲን መትከል የራስህ ፍራቻዎ ምንድን ናቸው?

5. ስለየትኛው የአገልግሎት ሁኔታ ነው ያንተ ባለቤትና/ ቤተሰብህ በጣም ስሜታቸው የሚነሳሳው?

6. ያንተ ባለቤትና የቤተሰብህ አባሎች መንፈሳዊ ስጦታቸው ምድን ነው?

7. የግል ባህርዬች፣ ስጦታዎችና ፍላጎቶች ሳንተ/ቺ ባለቤት የቤትሰ አባሎች እንዴት ነው በአገልግሎት ውስጥ ተሳትፏቸውን የሚወስነው?

8. ያንተ/ቺ ባለቤት ቤተሰብ ሲሳ ቃል የገቧቸው (ቤተሰብ፣ ሙያ ወይስ ሲሳ) ጉዳዩች ለሱ?

9. ያንተን/ቺን ባለቤት ቤተሰብ ተጨባጭ ካሆነ እና ሚዛናዊ ካልሆነ ይሆንልኛል ብለው ከሚጠብቁት ጉዳይ እንዴት ነው የምትከላከለው/ይው?

10. ከቤተሰብህ ጋር ተወያይተህ ወደ ስምነት የደረስክበት ስራ

- ወደቤት በሚደረጉ የስልክ ጥሪዎች
- የዕረፍት ቀን
- ስለበሊት ቀናቶች
- በቤት ውስጥ ስለሚኖር ቢሮ
- ከቤተክርስቲያን ጋር የተያያዙ በቤትህ ውስጥ የሚደረጉ መስተንግዶዎች

1.2መልሶችህን ከላይ ባሉት ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ሁለት ነገሮች ለማድረግ የፈለከውን ፃፍ

1. የበለጠ ራስህን ለመንከባከብ

2. ከቤተሰብህ/ሽ ጋር ግንኙነት ለማጠናከር

## አባሪ 1

## ምንባብ

## ሀ. ፀሎት

እኛ ዛሬ ስፀሎት እንዓዓስን እና ከፀሎት ደግሞ እንደበቃስን ወደእርሱ እንሳባስን በእርሱ ደግሞ እንገፈተራስን፡፡ ፀሎት ልናደርገው የተገባ ነገር እንደሆነ እናምናስን፡፡ ልናደርገው የተገናባ ነገር እንኳ ሆኖ ግን በመካላችእን ገደል ሆኖብናልል፡ እና በተግባር ግን እየፀስዷን ነው፡፡ ያስመፀስዴ ስቃዴ ግን እየተሰማን ነው፡፡ ም ወደኂሳ እንደሚደዘን ኛ በጣም እርግጠኛ አይደስንም፡፡ በእርግጥ በስራ በቤተሰብ ኃላፊነቶች ተጠምደናል፡፡ ነገር ግን ይህ መሸፈኛ ብቻ ነው፡፡ (---) አይደስም፣ ሌሳ ከዚህ የጠስቀ ነገር አስ፡፡ የበስጠ በጥልቀት ከቁጥጥሬ ስር ያዋስን ነገር አስ፡፡ የእውነት ከሆነ ብዙ ቁጥር ያሳቸው ነገሮች አሉ፡፡ ሁሳችንንም የከስከሉን እኛ በጊዜው ፈልገን የምንደርስባቸው ነገሮች፡፡ ስአሁኑ ግን አሁኑኑ ትኩረት ትኩረት የሚፈልግ አንድ ጉዳዩ አስ፡፡ እሱም “ሀሳብ” ነው፡፡ ስመፀስዴ ሲኖረን የሚገባ ነገር ሁሉ አስን ሁሉም “ትክክል” ነው ብስን ማሰንብ አስብን፡፡ ይህ በእውነት መፀስዴ ከመቻሳችን በፊት ነው፡፡ ሕይወታችን ጥቂት ሬቂቀ ማስተካያ ያስፈልጋታል ወይም የበስጠ እንዴት መፀስዴ እንዳስብን ማወቀቅ ያስፈልገናል፡፡ ወደ እኛ በፀሎት ዙሬ ያሉትን የፍልስፍና ጥያቄዎች ማጥናት ያስፈልገናል፡፡ ወይም እኛ የተሸ ስ ታስቀ ያፀሎት ልምምዶች ልንደዝ እና ሲኖረን ያስፈልገናል፡፡ እናም እንዲሁ ይቀጥሳል፡፡ እነዚህ የተሳሳቱ ጭንቀቶች አይደሉም ወይም በጭራሽ ስነሱ መፍትሄ ስመስጠት ጊዜ የስም አንልም፡፡ ነገር ግን እኛ የምንጀምረው ከነገሮች የተሳሳተ መጨረሻ ነው፡፡ ከፈረሱ በፊት ጋሪውን እናስወቀድማስን፡፡ የኛ ችግር ስስሒሳብና ስስመኪና ማስተማር ባደረግንበት መንገድ ፀሎትን ማስተማር የምናደርገው ነገር አድርገን እንገምታስን፡፡ እናም ብቁ የሆንነ እንደምንቀጣጠረው አድርጎ ከፍያስ ደረጃ ሳይ እኛን ያስቀምጠናል፡፡

ስፀልዴ ግን፡- በፀትታ እና ሆን ብስን ወደተማረክንበት በቁጥጥር ስር እና ብቁ ወዳስመሆን ዝቅ እንሳስን፡፡ የነገሬ እውነት ከተወሳሰቡ ብዙ ምክንያቶች ጋር ነው ወደፀሎት የምመጣው፣ ስሰው

መፅሐፍ ቅሱስን ማሰላሰል- አላማው ከእግዚአብሔር ጋር የወዳጅነት ውይይት ነው፡፡ ስለአንድ ቨርስ ወይም የመፅሐፍ ቅዱስ ትንሽ ክፍል ቀስ ብሎ በማሰብ ይታወቃል፡፡ ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የወዳጅነት ግንኙነት እና የግል ምላሽን ለቃሉ አጉልቶ ያሳያል፡

"ይን መቀበል ጥሩ ነው፡፡ እነዚህ ሶስቱ አቀራረቦች ለመፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣ ማጥናትና ማሰላሰል አንዱ ሌላውን አያስቀረውም፡፡ እንደ አንባው አላማ በመመስረት እያንዳንዱ ዋጋና ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህን ደግሞ ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ ሁሉም መፅሐፍ ቅዱስን የምናይበት መንገድ ለእግዚአብሔር ጅማሬ መልሱ ነው፡፡ በዕብራውያን መልዕክት 1፡1 ይን እናነባለን እግዚብሔር ከእኛ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ብዙ መንገዶች ተጠቅሟል፡፡ ይኸው መልእክት በምዕራፍ 4፡12 የሱ ቃል ሕያውና የሚሰራ የእግዚብሔርን ዘላለማዊ አላማዎች ለማሟላት ወደውስጥኛው የኛ አካል ዘልቆ እንደሚገባ ይነግረናል፡፡"

### ሐ. ቤተሰብ

ሁሉም ልጆች በወላጆቻቸው መፈቀርን እና ወላጆቻቸውን ማፍቀር ይፈልጋሉ (ይሻሉ)፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘረት አምስቱ ፍላጎቶች ለልጆች ተስማ ግንኙነት ከወላጆች ጋር እንዲኖራቸው ከነኚህ አንዳአንድ ባህርያት በቤተሰብ ግንኙነት ውስጥ ሲጎድሉ ፍቅር የመስጠትና የመቀበል ችሎታቸው ይጎዳል ወይም ውስን ይሆናል፡፡

- ደህንነት - እቤት ሲሆኑ ደህንነት ይሰማቸዋል
- አካልነት - የዚህ ቤተሰብ አካል መሆንህን መስማት ይቀበሉሀል ዋጋ ይሰጡሀል፡፡
- ገደቦች - በጠንካራና ፍቅር በተሞላ ስርዓት መተዳደር
- ህብረተሰብ - የጎረቤት ወይም የአካባቢው ህብረተሰብ ተግብቢ አባል መሆን
- የመላመድ ሕይወት - የመጫወት ዕድሎችና ሃሳብንና ስሜትን የመግለፅ ናቸው፡፡

## በትዳር ግንኙነት አፍራሽ የሕይወት አስተሳሰቦች

“በትዳርህ ተዋጋ” እንደሚለው መፅሐፍ እነኚህ አፍራሽ ግንኙነቶች የሕይወት አስተሳሰቦች የትዳርን ችግሮች ሊያባሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ማጋጋል፡- ንግግር ጀምሮ አሉታዊ ወደሆነ የጋራ ስሜት እያደገ ሲመጣ ይልቁንም በለስላሳ መልስ ምላሽ መስጠትና በእውነት አንዱ የሌላውን ስሜት መረዳት

ዋጋ ማሳጣት፡- አንድ ሰው የሌላውን ሰው ሀሳቦች፣ ስሜቶች የትዳር ጓደኛን ባሕርይ የሚያጣጥል የሰው አስተሳሰብን ዋጋ ማሳጣት ይባላል፡፡

አሉታዊ ትርጉም፡- ይህ ደግሞ የሚከሰተው የትዳር ጓደኛ እያንዳንዱን ንግግር ወይም ክስተት በከፋ መንገድ ስትረዳው ለአዎንታዊ መረዳት ምንም ቦታ ሳይኖረው ሲቀር ነው፡፡ እንደዚህ አይነት አሉታዊ ትርጉሞች የትዳር ጓደባን አሳማ ምን እንደሆነ ወደመፈተሽ ያመራሉ፡፡

መውጣት/መሸሽ፡- ብዙውን ጊዜ የትዳትር ጓደኛ የተወሰኑ ርዕሶች ወይም ይከታተሳሉ ሌሳኛው ከርዕሱ ይወጣል ከውይይቱ ይሸሻል፡፡ ጥንዶች ለግጭቶች መፍትሔ በመስጠት ጥረት በማድረግ ከምር ካልተሰማረ ለግጭቶች መልካም መፍትሔ መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡

የማይለዋወጡና የሚለዋወጡ ምክንያቶች

የተጋቡ ጥንዶችን ለመለያየት እየጨመረ የሚሔዱ ዝንባሌዎች

“ለትዳርህ ተዋጋ” እንደሚለው መፅሐፍ ከዚህ በታች የተዘረዘረት ከምክንያቶቹ አንዳንዱ ሲሆኑ የጋብቻ ግጭቶችን ሊያባብሱ የሚችሉና ጫና ከመፍየራቸውም በላይ ለመለያየትና አንዳንዱም ለፍቺ ይዳርጋሉ፡፡

### የማይለዋወጡ ምክንያቶች

- እጅግ በጣም ጠንካራ ምላሽ ለችግሮች የሚሰጥ ባህርይ
- በፍች ሂደት ያሉት ወላጆች /ወላጆች የተፋቱበት

- ከጋብቻ በፊት የፍቅር ግንኙነቶች የነበረው ከሆነ
- በፍች ውስጥ ያሉት /ፍች ያደረጉ
- ከሌላ ጋብቻ ልጅ ያላቸው
- የታወቀ የተለያየ መነሻ እና ሃይማኖታዊ ልማዶች
- በጣም በልጅነት እድሜ ጋብቻ መፈፀም
- ከጋብቻ በፊት እርስ በእርስ በደንብ አለመዋወቅ
- ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግሮች

**ተከዋዋጭ ምክንያቶች**

- አሉታዊ የንግግር ዘይቤ እና መደባደብ
- ግጭቶችን በማስተዳደር መቸገር
- ተጨባጭነት የሌለው በጋብቻ ውስጥ በማግኘት የሚጠበቁ ነገሮች
- የጥንዶቹ ዝቅ ያለ የመሰጠት ደረጃ
- በአንድ ላይ የእምነት ሕይወት አለመለማመድ

**መ. የወንጌል ስብከት ስርጭት**

ወብጌልን የማሰራጨት ስልት እና በውጤታማነት አማኞችን መከታተል ወንጌልን ለማሰራዐጨት ውጤታማነታቸው የተረጋገጠ ብዙ ሞዴሎች አሉ፡፡ ከእነርሱ አንዱ "ፕሮጀክት ፊልን" ነው፡፡ ይህ በጣም ቀላል ስልት ነው በአለም ዙሪያ በሺህ የሚቆጠሩ ቤተክርስቲያኖች ፈድቷል፡፡ ይህንም ለማድረግ የዩሐንስ ወንጌልን ኮፒ ለአንድ ሰው ከጥናት መመሪያ ጋር ለአምስት ሳምንቶች መስጠት ይሆናል፡፡ ከሰውየው ጋር በምትገናኙበት ጊዜ ቃሉን በጋራ በምታጠኑበት ጊዜ፣ ወንጌሉን ስታበስር እና አብረህ ስትፀልይ ከእርሱ ጋር ግንኙነትህን ታዳብራለህ፡፡ ለመጀመሪያው ጥናት በኋላ ሰዎች በቡድን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ፡፡ ብዙ ሰዎች ቤተክርስቲያንን የተቀላቀሉት በዚህ መንገድ ነው፡፡ ፕሮጀክት ፊሊፕ ደግሞ ለክትትል እና መፅሐፍ ቅዱስን

ማዕከላዊ ሳደረገ መፅሐፍ ቅዱስን ማዕከላዊ ሳደረገ የደቀመዛሙርትነት ማቴሪያል ያቀርባል፡፡ እና ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ ስጦታዎችን ይሰጣል፡፡

ለዚህ አጠር ያሉ ምሳሌዎችን እናቀርባለን

ፕሮጄክት ፊሊጶስ ምንድን ነው? ለአካባቢ ቤተክርስቲያን እድገት የወንጌክል ስርጭትና ደቀማዛሙርት የማፍርያ ስልት ነው፡፡ የዚህ ስልት የመፅሐፍ ቅዱስ መሰረቱ የሐዋርያት ስራ 8፡26-40 ነው፡፡ በፊጶስ እና በኢትዮጲያዊቷ ጃንደረባ መካከል ባለው ታሪክ እንዴት እንደተገናኙ እና ሰዎችን ለክርስቶስ ስለመድረስ ሶስት መርሆች ያስተምረናል፡፡

1. የወንጌል ስርጭት፡- የእግዚአብሔርን ቃል በሰዎች እጆች ላይ ያስቀምጣል ኢትዮጲያዊው ጃንደረባ የእግዚአብሔርን ቃል ከኢሳያስ መፅሐፍ እያነበበ እያለ የበለጠ ለማወቅ እንደፈለገ ተሰማው
2. ደቀመዛሙርት ማድረግ፡- አዲሱን አማኝ መከታተል ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ በኢሳያስ ያለውን ምንባብ አብራርቶልናል ከዛም ወንጌልን ለእርሲሱ አብስሮታል፡፡
3. አባልነት፡- ሰውየውን ለቤተክርስቲያን ቃል እዲገባ ማሳመን፤ ፊሊጶስን ከሰማ በኋላ ኢትዮጲያዊው መጠመቅ እንዲችል ጠየቀ፡፡ በዚህ መንገድ ወደክርስቶስ አካልነው ተጨመረ፡፡

**የዩሐንስ ወንጌል ጥናት**

በዘመቻ ፊሊጶስ የሰለጠነው ስልታዊ በሆነ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ደግመው ሊያገኟቸው ሳቀዱ ሰዎች በጥንቃቄ ሰጥተዋል፡፡

ግቡ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያውቁ እናም ለቤተክርስቲያን ራሳቸውን እንዲሰጡ ነው፡፡ ይህ የመጀመሪያው ትምህርት “በዝርዝር ወደማጠቃለያ” የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ከወንጌሎች አንዱን ለማጥናት ግብዣውን ለተቀበሉ ሰዎች የሚጠቅም ነው፡፡

- 5 ደቂቃዎች፡-  የሚከተሉትን ጥያቄዎች የዩሐንስ ወንጌልን ብ በመጠቀም ከጥያቄዎቹ በኋላ እንደተሰጠህ የመፅሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎች መሰረት መልስ ስጥ
- 15 ደቂቃዎች፡- ጥያቄዎቹን ከመስስክ በኋላ መልስህን ለሌሎች ለማካፈል ሁለት ወይም ሶስት ሰዎችን አግኛቸው እያንዳንዱን ሰው ቡድኑን በመምረጥ የግዴታ ተራ ይድረሰው።

የመጀመሪያ ሳምንት፡- ትምህርት አንድ (ምዕራፍ 1-5)

1. ማነው ሕይወትን የፈጠረው እና ለሕዝቡ ብርሃን የሆነው ማን ነው? (1፡4)
2. የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን መብት ለማግኘት እኛ ምን ማድረግ አለብን? (1፡12)
3. በማን ነው የእግዚአብሔርን ፍቅሩንና እውነቱን የምናውቀው? (1፡17፣18)
4. ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ለአለም እና ደግሞ ለአንተ ያደረገው ምንድን ነው? (1፡29)
5. የመጀመሪያውን የሱን ታምራት በማድረግ ኢየሱስ ምን አሳየ? (2፡11)
6. በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ለመሆን ምን ማድረግ አለብን ? (3፡3)
7. እኛን ነማዳን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለምን ሰጠ?(3፡16-18)
8. ለእነርሱ በኢየሱስ ለሚያምኑት ምን ይኖራቸዋል? ብትክደው ምን ይሆናል? (3፡36)
9. የሰማርያ ሰዎች ከሱ ጋር ጊዜ ከወሰዱ በኋላ ስለኢየሱስ ምን አወቁ? (4፡40-42)
10. የኢየሱስን ቃሎች ሰምተህ ብታምናቸው ምን ይሆንልሀል? (5፡24)

ማስታወሻ፡- የአንተ ቤተክርስቲያን የራሷን ጥያቄዎች ከወንጌሎች ከአንዱ ልታዘጋጅ ትችላለች ሺዎች ወደክርስቶስ የመጡት በዚህ መንገድ ነው።

# አባሪ 2

ስድስት የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች

1. የፊት ለፊት

የመልዕክቱ ጭብጥ ያለበት ቁጥር 2ጢሞ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ጴጥሮስ ሐዋ 2፡14-23

የዘመናችን ምሳሌዎች ቢል ግርሃምና ሉዊስ ፓውሎ በባህርያቸው በራስ የሚተማመኑ ደፋር፣ብርቱ፣ ግልፅና ታማኝ ናቸው፡፡

በንግግሮች ጊዜ ወደዋናው ሃሳብ ነው የሚያተኩሩት፡፡ ጠንካራ እምነት እና የግል አስተያየት ነው ያላቸው፡፡

ቅድመ ጥንቃቄ፦ ሌሎችን ለመርዳትና ጠንቃቃ እንድትሆን የእግዚአብሔርን ጥበብ ጠይቅ አቀራረብህን ለስላሳ እንዲያደርገውና በሚያስፈልግ ጊዜ የፀና እምነትህን እንዲያጎላው ለመንፈስ ቅዱስ ፍቀድለት፡፡ ሌላ የወንጌል ስርጭት ዘዴዎች በሚጠቀሙት ላይ አትፍረድባቸው፡፡

2. ምሁር

የመልዕክቱ ጭብጥ ያለበት ቁጥር፦ 2ኛ ቆሮ 10፡5 የመፅሐግ ቅዱስ ምሳሌ ጳውሎስ ሐዋ 17፡18፣22

የዘመኑ ምሳሌ፦ ጆሽ ማክዶዌል

ባህርያት፦ ነገሮችን መተንተን ትወዳለህ በጣም ሎጂካል ነህ ጉጉ እና ጥያቄ መጠየቅ ትወዳለህ አንተ መከራከር ትወዳለህ

ቅድመ ጥንቃቄ፦ በምሁሩናን ክርክር ውስጥ እብዳትዋጥ ተጠንቀቅ

አስታውስ፡- ያንተ አቀራረብ የሚያስፈልገው እንደ ጠቃሚ መረጃ ነው፡፡ 1ኛ ጴጥ 3፡16 የሚለው በጨዋነት እና በአክብሮት ልንመልስ እንደሚገባ ነው፡፡ ተከራካሪ እንዳትሆንና በውዝግብ እንዳትጠላለፍ ተጠንቀቅ፡፡

3. ምስክርነት

የመልዕክቱ ጭብጥ ያለበት ክፍል 1ኛ ዩሐ 1፡1-4 መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው ዩሐ 9፡10፣15

የዘመናችን ምሳሌዎች፡- ኒኪ ጋርዛ፣ ኮሪ ቲን ቡም፣ ጆኒ ኤርክሰን

ባህርያት፡- ጥሩ ተግባቢና ተናጋሪ ነህ ስለግላዊ ሕይወትህ ስለምትጨነቃቸው ነገሮች እና ስለስኬትህ ለሌሎች ከመናገር ግልፅ ነህ፡፡ እግዚአብሔር በህይወትህ ስለሰራው ትደነቃለህ ባንተና በሌሎች ሰዎች መካከል ያለውን የልምድ ዝምድና ታያለህ፡፡

ቅድመ ጥንቃቄ፡- ያንተን ልምዶች ከሚያዳምጥህ ሰው ሕይወት ጋር ለማዛመድ እርግጠኛ ሁን፡፡ የሌላውን ሰው ሕይወት ካንተ ሕይወት ጋር ለማዛመድ አንተ በመጀመሪያ ብዙ ከሰውየው እንድታደምጥና ብዙ እንድታውቅ ካንተ ይፈልጋል፡፡ ያንተን ልምዶች ዋጋቸው ምንም እንኳን ተራ ቢሆኑም ዝቅ አድርገህ አትገምታቸው፡፡ የተለመዱ ታሪኮች ከብዙሃኑ ሕዝብ ጋር ለማዛመድ የሚችሉ ናቸው፡፡

4. በግል (አንድ ለአንድ)

የመልዕክቱ ጭብጥ ያለበት ቁጥር 1ቆሮ9፡22 መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ማቴዎስ ሉቃ 5፡27-29

የዘመኑ ምሳሌ፡- ጆይ ሊልድሮች "የሕይወት ዘዴ የወንጌል ስርጭት" ን መፅሐፍ ፀሐፊ

ባህርያት፡- ማውራት ትወዳለህ አንተ የምትራራና ሌሎችን የምትረዳ ነህ ጓደኝነትን ትፈልጋለህ፡፡ በሰዎችና በፍላጎታቸው ላይ ታተኩራለህ፡፡

ቅድመ ጥንቃቄ፡- ከእውነት ይልቅ ለጓደኝነት ዋጋ አትስጥ ኃጥያተኞች እንዲሆኑ እና አዳኝ እንደሚያስፈልጋቸው ጓደኞችህን ልታስጠነቅቃቸው ያስፈልጋል፡፡ ስለጓደኞችህ ፍላጎቶች እጅግ በጣም አትጨነቅ የምትችለውን ያህል እርዳቸው የቀረውን ለጌታ ተወው፡፡

5. በግብዣ /በጥሪ

የመልዕክቱ ጭብጥ ያለበት ቁጥር፡- ሉቃ14፡23

መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ከውሃ ጉድጓድ ልትቀዳ የመጣችው ሴትዩ

የዘመኑ ምሳሌ፡- ረት ግራሃም

ባህርያት፡- አንተ እንግዳ ተቀባይ እና ሌሎችን ማሳመን የምትችል ነህ አዲስ ሰዎችን መገናኘት ደስ ይልሀል፡፡ የወንጌል ስርጭት ዝግጅቶችን እንደ ልዩ እድሎች ነው የምታየው፡፡

ቅድመ ጥንቃቄ፡- ተጠንቀቅ በአንተ ፈንታ ሌሎች እንዲናገሩ ሁልጊዜ አትፍቀድ የአንተ ጓደኞች እና የምታውቃቸው ሰዎች እንዴት ክርስቶስ እንደለወጠህ ካንተ ሊሰሙ ይፈልጋሉ፡፡ በተጨማሪም የአንተ ጓደኞች አንተ ልትመልስላቸው የምትችለውን ወንጌል በሕይወታቸው ለላለው ጠቀሜታ ጥያቄ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በየትኛው የወንጌል ስርጭት ዝግጅቶች ወይም አገልግሎቶች ሰዎችን ልትጋብዝ የምታስበውን በጥንቃቄና በፀሎት አመዛዝን፡፡ ቢንቁህ ቅር ልትሰኝ የነሱ አስመወበል ስመንፈሳዊ ውይይት እድል ይከፍታል፡፡ ደግሞ የነሱ የዛሬ እምቢ ማለት የነገ እሺ ሊሆን ይችላል፡፡

6. አገልግሎትን ያማከለ፡- ተግባራዊ የፍቅር አገልግሎትን ለመቃወም ወይም ለመጣለት አስቸጋሪ ነው፡፡ የመልዕክቱ ጭብጥ ሃሳብ ያለበት ክፍል ማቴ 5፡16 መፅሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ዶርቃ ሐዋ 9፡33-35

የዘመኑ ምሳሌ፡- እናት ቴሬዛ

ባህርያት፡- ታጋሽ ነህ፣ በሌሎች ሰዎች ላዎች ላይ አጅግ ታተኩራለህ የሰዎች ፍላጎቶችን ታያለህ ፍላጎታቸውን በማሟላትህ ከቃላት ይልቅ ፍቅርህን የበለጠ በተግባሮችህ ታሳያለህ፡፡ አንተ በትጋት ዝቅተኛ ተግባሮችን በትህትና ትፈፅማለህ፡፡

ቅድመ ጥንቃቄ፡- አስታውስ መልካም ቃሎች መልካም ተግባር ከሌላቸው ግራ ያጋቡናል፡፡ ስለዚህ ጥሩ ተግባሮችን ያለገለፃ አድርጋቸው፡፡ ሮሜ 10፡14 ስለኢየሱስ እንድንናገር ይገባል ሌ.ሎች እንዲሰሙ፡፡ የአገልግሎትህን የተግባሮችህን ዋጋ ዝቅ አድርገህ አትገምታቸው፡፡ የአንተ ዘዴ ከእግዚአብሔር የራቁትን በእርሱ የተቆጡትን ሊደርሳቸው ይችላል፡፡

## አባሪ 3

እንግዳን መቀበል ፡-

ቤተክርስቲያንን የበለጠ እንግዳ ተቀባይ ማድረግ፡፡ የሚበዙት አለም የሚጠቀምባቸው የመገናኛ ዘዴዎች ካጥያት አይደለም እናም በቤተክርስቲያን መጠቀም ይገባል፡፡

“በአንዳንድ ቤተክርስቲያኖች ወንጌልን ለማድረስ ከሚጠቀሙበት ዘዴዎች ይልቅ ለማያምን ሰው የክርስትስ መስቀል በጣም አበስተኛ ጥቃት ነው፡፡” (Knute Larson)

“አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በአንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ አንሰጥም ነገር ግን በሁሉ እንደእግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናገኛለን፡፡” 2ኛ ቆሮ 6፡3፣4

"ሰባ ከመቶ የኛን ቤተክርስቲያን ከጎበኙት መካከል፣ ፓስተሩ ለመስበክ ከመቆሙ በፊት ለመመለስ ወይም ላለመመለስ ውሳኔ ያደርጋል፡፡" (ባርና የጥናት ቡድኑ)

ከዚህ በታች ለአሁድ የአምልኮ አገልግሎቶች ባጠቃላይ ለቤተክርስቲያን የሚያስፈልጉ ዝርዝር መሰረታዊ ነገሮች ታገኛለህ፡፡ አንተ ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ልትጨምር ትችላለህ ይህን መልመጃ ስትሰራ በአዲስ ሰው ቦታ ራስህን ለማስቀመጥ ጥረት አድርግ እና ለመጀመሪያ ጊዜ እንደአየህ ሆነህ ነገሮችን ተመልከት፡፡

1. ምልክቶች

- ምልክቶች ሽንትቤት፣ የህፃናት ማቆያ፣ የመኪና ማቆሚያ የት እንዳሉ የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው፡፡
- ትልቅና ግልፅ በሆኑ ፊደሎች
- ዘመናዊ የቤተክርስቲያን አርማ
- ______________________________________
- ______________________________________

2. አገልግሎት

- ንፁህና የሚያስደስት
- ሽንት ቤቶች ንጹህ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ የቀረቡበት በፊት በመሃል እና ከአገልግሎት በኋላ
- የመኪና ማቆሚያ ብዙና ለማግኘት ቀላል
- የውጭ አካባቢው በደንብ ያማረ
- ____________________________________
- ____________________________________

3. አስተናጋጆች እና አቀባበል

- ሰው ወዳድና መረጃ በደንብ ያላቸው
- ወንድና ሴት አስተናጋጅ ሚዛናቸው የተጠበቀ
- ከተለያዩ እድሜ የተወከሉ
- ____________________________________
- ____________________________________

4. የህፃናት መንከባከቢያ ቦታ

- የደህንነቱ ስርዓት የተረጋገጠ
- የሰለጠኑ ሰራተኞች
- ስርአረን የሚያብራራ እትም

________________________________________

________________________________________

5. አጠቃላይ ሁኔታ

- የማጀቢያ ሙዚቃ
- ጥሩ ብርሃን
- የማስዋብ ስራ
- የሚመች መቀመጫና ለመግባት እና ለመውጣት ምቹ

________________________________________

________________________________________

6 የአምልኮ መሪዎች የምስጋና መሪዎች መጋቢ ወ.ዘ.ተ

- የጋሉ እና በትጋት የሚያገለግሉ
- እውነተኛ
- በሚገባ የሰበሉ
- ______________________________
- ______________________________

7. ቋንቋ

- ግልፅ (ለቤተክርስቲያን ቋንቋ ጥንቃቄ አድርግ)
- አቃፊ
- ______________________________
- ______________________________

8. ሙዚቃና ዝማሬ

- የሳቀ ሙዚቃ
- የዝማሬዎቹ ስነመለኮታዊነት
- በዝማሬው ውስጥ ግልፅና የሚሰሙ ቃላቶች
- ______________________________
- ______________________________

9. የአምልኮ አገልግሎት ስርአት

- የተደራጀ
- በስርአቱ የሚጀምርና በትክክል የሚቀጥል
- የተለያዩ (ድራማ እና ቪዲዮ ወ.ዘ.ተ)

10. የታተሙ ፅሑፎች

- በደንብ የተፃፋ (ግልፅ እና በቀላሉ የሚነበብ)
- የቃላት አፃፃፋ ስህተት የሌለበት
- ______________________________
- ______________________________